# 10

# ነቢያት፡
# በእስራኤል የቃል ኪዳን አስከባሪዎች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትንቢትን ርእስ ይዘው የሚመጡ መጻሕፍት ከሌሎቹ ሁሉ በላይ በቁጥር በርከት ብለው እናገኛቸዋለን። አራቱ ዐበይት ነቢያት (ኢሳይያስ፥ ኤርምያስ፥ ሕዝቅኤልና ዳንኤል) እንዲሁም አሥራ ሁለቱ ንዑሳን ነቢያት (አሥራ ሁለቱ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻ መጻሕፍት) ከእግዚአብሔር ዘንድ ብዙ መልእክቶችን አምጥተዋል። እነዚህም የነቢያት መጻሕፍት የተጻፉት ከ760 እስከ 460 ዓ.ዓ. ባለው የጥንታዊቷ እስራኤል ዘመን ነበር። ንዑሳን ነቢያት የሚለውን ሐረግ የምንጠቀምበት ምክንያት እነዚህ መጻሕፍት ከሌሎቹ በገጽ ብዛት አጠር ብለው ስለሚገኙ ብቻ ነው። ዐበይት ነቢያት በአንጻራዊነት ሰፋ ያሉ መጻሕፍት ናቸው። «ዐቢይ» «ንዑስ» የሚሉ ቃላት ከአስፈላጊነት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም።

## የትንቢት ባሕርይ

የትንቢት መጻሕፍት ለማንበብም ሆነ ለማጥናት እጅግ አስቸጋሪዎች መሆናቸውን ከወዲሁ መግለጹ አስፈላጊ ነው። እነዚህን መጻሕፍት በተሳሳተ መንገድ የምንረዳባቸው ምክንያቶች ደግሞ ከአገልግሎታቸውና ከቅርጻቸው ጋር የተያያዙ ናቸው። ነገር ግን ስለ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ከመነጋገራችን በፊት አንዳንድ አስተያየቶችን ማስቀደም ይኖርብናል።

### *የትንቢት ምንነት*

ብዙዎቹን የአሁን ዘመን አንባብያን የሚያጋጥመው የትንቢት ቀዳማይ ችግር «ትንቢት» ለሚለው ቃል በአእምሯቸው ውስጥ ከተቀረጸው የተሳሳተ ግንዛቤ የሚመነጭ ነው። አብዛኞቹ ሰዎች ትንቢትን የሚገነዘቡት ብዙዎቹ መዝገበ ቃላት በመጀመሪያው ረድፍ ከሚያስቀምጡት ብያኔ የተለየ አይደለም። ይህም፥ «ወደ ፊት የሚሆነውን ቀድሞ መናገር» የሚል ነው። ከዘመናቸው በኋላ ወደ ፊት የሚፈጸሙትን ነገሮች መተንበይ የነቢያት ዋንኛ ትኩረት ይመስል ብዙ ክርስቲያኖች ትንቢትን ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ወይም አንዳንድ የአዲስ ኪዳን ዘመን ገጽታዎች አድርገው ይወስዳሉ። ነገር ግን ነቢያት በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙም ትኩረት እንዳላደረጉ መገንዘብ ተገቢ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ እስኪ ይህንን አኃዛዊ መረጃ

ተመልከት። የብሉይ ኪዳን ትንቢት መሚሐዊ ይዘቱ ከሁለቱ በመቶ በታች ነው። ስለ አዲሱ ቃል ኪዳን ዘመን በግልጽ የሚናገረው ከአምስት በመቶ ያንሳል። ገና ወደ ፊት ስለሚሆኑት ነገሮች የሚናገረው ደግሞ ከአንድ በመቶ ያንሳል።

በእርግጥ ነቢያት ስለ ወደፊቱ ዘመን መናገራቸው እውነት ነው። ነገር ግን እነርሱ የተነበዩለት የወደፊት ዘመን እኛን የሚመለከት ሳይሆን፥ የእስራኤልን፥ የይሁዳንና የሌሎችንም በአካባቢያቸው የሚገኙትን አገሮች የቅርብ ጊዜ ታሪክ የሚተነብይ ነው። ስለሆነም ትንቢቶችን ለመረዳት ከሚያስፈልጉት ቁልፎች አንዱ ትንቢቶቹ ተፈጽመው እንዳለፉ መገንዘብ ነው። ወደ ኋላ ተመልሰን ለእነርሱ ገና የወደፊት፥ ለእኛ ግን ያለፉትን ጊዜያት መመልከት ይኖርብናል።

*ነቢያት እንደ ቃል አቀባዮች*

ነቢያት ወደፊት የሚፈጸሙትን ክስተቶች ተንባዮች ናቸው ማለቱ ቀዳማይ አገልግሎታቸውን እንድናጣ ያደርገናል። ይህ ቀዳማይ አገልግሎታቸው በዘመናቸው ለነበሩት ሰዎች የእግዚአብሔርን መልእክት ማስተላለፍ ነበር። የግንዛቤ ችግሮቻችንን የሚያባብሱት ደግሞ የትንቢቶቻቸው የቃላዊነት ባሕርያት ናቸው።

ለምሳሌ፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን በጥንታዊቷ እስራኤል ውስጥ ከነበሩት በመቶዎች ከሚቆጠሩ ነቢያት መካከል በመጻሕፍት መልክ ተሰብስበው የሚጻፉ መልእክቶችን ከእግዚአብሔር ተቀበለው ለሕዝቡ እንዲያስተላልፉ የተመረጡት አሥራ ስድስቱ ብቻ ናቸው። እንደ ኤልያስና ኤልሳዕ ያሉ ሌሎች ነቢያትም የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡና ለሌሎችም በማስተላለፉ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ እናውቃለን። ነገር ግን ይበልጥ የምናውቀው ቃላቸውን ሳይሆን ነቢያቱ ራሳቸውን ነው። ከተናገሩት በላይ በተግባር ያደረጉት በስፋት ተዘግቦአል። የተናገሩትም ቢሆን በብሉይ ኪዳን ተራኪዎች አማካኝነት በግልጽ የሰፈረው በዘመናቸው ዓውድ ውስጥ ነበር። እንደ ጋድ (1ኛ ሳሙ. 22፤ 2ኛ ሳሙ. 24፤ ወዘተ...)፥ ናታን (2ኛ ሳሙ. 7፥ 12፤ 1ኛ ነገ. 1፤ ወዘተ...)፥ ወይም ሁልዳ (2ኛ ነገ. 22) ያሉት ነቢያት ትንቢትና የግል ታሪክም አብሮ ቀርቧል። ይህም ከዮናስና በአነስተኛ ደረጃ ከዳንኤል ሁኔታ ጋር የሚመሳሰል ነው። የብሉይ ኪዳን የትረካ መጻሕፍት በአጠቃላይ ስለ ነቢያት የሚነግሩን ሲሆን፥ ከነቢያቱ ከራሳቸው የምንሰማው ግን በጣም ጥቂት ብቻ ነው። በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ ግን በነቢያቱ በኩል ስለ እግዚአብሔር እንድንሰማ ይደረጋል። ከነቢያቱ ከራሳቸው ግን ብዙም የምንሰማው የለንም። ሰዎች

የብሉይ ኪዳንን ትንቢታዊ መጻሕፍት እንዳይገነዘቡ ብዙውን ችግር የሚያስከትለው ይኸው አንድ ልዩነት ነው።

በተጨማሪም፥ ረዣዥሞቹን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአንድ ቁጭታ አንብቦ መጨረሱ አስቸጋሪ መሆኑን አስተውለህ ታውቃለህ? ለምን እንደዚያ ሆነ ብለህ አሰብህ? በመጀመሪያ ደረጃ፥ ምናልባትም ለዚህ ደረጃ አልታቀዱም ይሆናል ብለን እናስባለን። በአብዛኛው እነዚህን ረዣዥም መጻሕፍት የቀድሞ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የቀረቡ ሳይሆኑ የተነገሩ የእግዚአብሔር መልእክቶች ስብስብ ናቸው። የእነዚህን መልእክቶች ታሪካዊ መቼት መረዳቱ አስቸጋሪ ሲሆን፥ አንደኛው አልቆ ሌላው የሚጀምርበት ስፍራም ፍንጭ አልተሰጠበትም። በተጨማሪም፥ ብዙዎቹ መልእክቶች የተነገሩት በግጥም ስልት ነው። ከዚህ በታች ስለዚህ ጉዳይ ሰፋ ያለ አሳብ እናቀርባለን።

### *የታሪክ ችግር*

ስለ ትንቢቶች ያለንን ግንዛቤ የሚያወሳስበው ሌላው ነገር ታሪካዊ ርቀት ነው። ከነገሮች ባሕርይ ሳቢያ ያን ጊዜ ከነቢያቱ በጆሯቸው ከሰሙት እስራኤላውያን ይልቅ፥ በዛሬው ዘመን ያለን እኛ የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት እንቸገራለን። ለእነርሱ ግልጽ የነበሩት ነገሮች ለእኛ ይደበዝዛሉ። ለምን? በተናጋሪው ዓውድ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የተናጋሪውን ቃላት በሁለተኛ ደረጃ በጽሑፍ ከሚያገኙት የበለጠ ጥቅም አላቸው። (በምዕራፍ 8 ስለ ምሳሌዎች ከተነገረው አሳብ ጋር አነጻጽር)። ነገር ግን አብዛኛው ችግር የሚመጣው ከዚህ አይደለም። ነገር ግን ሰዎች ከጥንታዊቷ እስራኤል ሃይማኖታዊ፥ ታሪካዊና ባሕላዊ ሕይወት እየራቁ ሲሄዱ፥ በነቢያት የተነገሩትን ቃላት በተገቢው ዓውዳቸው የማስቀመጥ ችግር ያጋጥመናል። ብዙውን ጊዜ ቃላቱ ምንን እንደተመለከቱ ለምንስ እንደሚያመለክቱ ማወቅ ይሳነናል።

## የትንቢት አገልግሎት

እግዚአብሔር በእነዚህ የተጻፉ ቃላት ምንን እንደሚነግረን ለመረዳት በእስራኤል የነቢይ ሚናና አገልግሎት ምን እንደሆነ ማወቅ አለብን። በዚህ ረገድ በሦስት ነገሮች ላይ ማተኮር ይኖርብናል።

ነቢያት በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የቃል ኪዳን አስፈጻሚ መካከለኞች ነበሩ። የእስራኤል ሕግ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል እንዴት ቃል ኪዳንን እንደ መሠረተ ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ አብራርተናል። ይህ ቃል ኪዳን ሕዝቡ የሚጠብቋቸውን ደንቦች ብቻ ሳይሆን፥ ደንቦቹን ቢተላለፉ የሚያጋጥሟቸውና ቅጣቶችና ደንቦቹን

ቢጠብቁ ደግሞ የሚያገኟቸውን ጥቅሞች ጭምር ይዘረዝራል። ብዙውን ጊዜ ቅጣቶቹ የቃል ኪዳን «መርገሞች»፥ ጥቅሞቹ ደግሞ «በረከቶች» በመባል ይታወቃሉ። ስያሜው አስፈላጊ አይደለም። አስፈላጊው ነገር እግዚአብሔር ሕጉን ሰጥቶ ብቻ ዝም እንደማይልና ተግባራዊ እንደሚያደርገው ነው። አዎንታዊ አተገባበር በረከትን ሲያመጣ፥ አሉታዊ አተገባበር ግን መርገምን ያስከትላል። ችግሩ የሚመጣው እዚህ ላይ ነው። እግዚአብሔር የሕጉን (አዎንታዊ ወይም አሉታዊ) አፈጻጸም የገለጸላቸው፥ ሕዝቡ የበረከትን ወይም የመርገምን ክስተቶች በትክክል እንዲያውቁ ነበር። እግዚአብሔር መጀመሪያ ሕጉን በሰጠ ጊዜ ሙሴ መካከለኛ ሆኖ ስላገለገለ የነቢያት ሞዴል ነው። ነቢያት ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መካከለኞች ወይም ቃል አቀባዮች ናቸው። እግዚአብሔር ከሙሴ በኋላ ለነበሩት ትውልዶች ሕጉን ከጠበቁ እንደሚባረኩና ካልጠበቁ ግን እንደሚረገሙ በነቢያት በኩል ገልጾላቸዋል።

እስራኤላውያን ለቃል ኪዳኑ ታማኞች ቢሆኑ የሚያገኙዋቸው በረከቶች በተለይ በዘዳግም 4:32-40 እና 28:1-14 ተገልጸዋል። ነገር ግን እነዚህ በረከቶች የታወጁት ከማስጠንቀቂያ ጋር ነው። እስራኤል ለእግዚአብሔር ሕግ ባትታዘዝ በረከቶቹ ይነጥፋሉ። እስራኤል የእግዚአብሔርን ሕግ ብትተላለፍ የምትቀበላቸው መርገሞች (ቅጣቶች) በተለይም በዘሌዋውያን 26:14-39፤ ዘዳግም 4:15-28 እና በዘዳግም 28:15-32:42 ውስጥ ይገኛሉ።

ስለሆነም ነቢያት የሚያውጁቸውን በረከቶች ወይም መርገሞች ራሳቸው አፍልቀው እንደማይናገሩ መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። መንፈስ ቅዱስ በመራቸው መንገድ እነዚህን በረከቶችና መርገሞች ስሜትን በሚነካ መንገድ ሊያቀርቡ ቢችሉም፥ ቃሉ የእግዚአብሔር እንጂ የራሳቸው አይደለም። እግዚአብሔር በእነርሱ አማካኝነት ቃል ኪዳኑን ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚፈልግ ገልጾአል። ይህም የቃል ኪዳን አፈጻጸም በእስራኤል ታማኝነት ላይ ተመሥርቶ ለጥቅሙ ወይም ለጉዳቱ የሚውል ይሆናል። ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን በዘሌዋውያን 26፥ ዘዳግም 4 እና ዘዳግም 25-32 ላይ በሚገኙት የበረከትና የእርግማን ምድቦች ላይ በመመሥረት ነው። እነዚህን የፔንታቱክ ምዕራፎች ብታጠና ነቢያት እነዚያን ነገሮች ለምን እንደተናገሩ በበለጠ ትገነዘባለህ።

በአጭሩ አንድ ሰው የሚያገኘው ግንዛቤ ይኼ ነው። ሕጉ ቃል ኪዳኑን በታማኝነት ለሚጠብቁት የሚሰጣቸው በረከቶች አሉ። እነዚህም ሕይወት፥ ጤንነት፥ ብልጽግና፥ የእርሻ መትረፍረፍ፥ አክብሮትና ከአደጋ መጠበቅ ናቸው። ከተጠቀሱት በረከቶች አብዛኞቹ

ከስድስቱ አጠቃላይ ምድቦች በአንዱ ውስጥ ይውላሉ። መርገሞችን አስመልክቶ ሕጉ እንደ ሞት፥ በሽታ፥ ድርቅ፥ ጉድለት፥ አደጋ፥ ውድመት፥ ሽንፈት፥ ወደ ሌሎች አገሮች መሰደድ፥ ማጣትና መጎሳቆል የመሳሰሉትን ነገሮች ይዘረዝራል። አብዛኞቹ መርገሞች ከእነዚህ መካከል በአንደኛው ምድብ ውስጥ የሚውሉ ናቸው።

እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካኝነት በሚያስተላልፈው መልእክት ውስጥ እነዚህ ምድቦች አገልግሎት ይሰጣሉ። ለምሳሌ፥ (ለአንድ ግለሰብ ሳይሆን) ለሕዝቡ ወደፊት ስለሚመጣው በረከት በነቢዩ አሞጽ አማካኝነት ለመተንበይ ሲፈልግ ይህንኑ ያደረገው የእርሻን መትረፍረፍ፥ ሕይወት፥ ብልጽግና፥ ክብርና ከአደጋ መጠበቅ በሚገልጹ ዘይቤዎች ነበር የተጠቀመው (አሞጽ 9፡11-15)። በሆሴዕ ዘመን በነበሩት የማይታዘዙ እስራኤላውያን ላይ ስለሚመጣው ጥፋት ሲተነብይ ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት የመርገም ዓይነቶች አንዱን ወይም ሁለቱን ተጠቅሟል (ለምሳሌ፥ በሆሴዕ 8፡14 ውድመት፥ በ9፡3 ወደ ሌሎች አገሮች መሰደድ)። ምንም እንኳ ቀጥተኛ ፍች ሊኖራቸው ቢችልም፥ እነዚህ መርገሞች ብዙውን ጊዜ ዘይቤያዊ ናቸው። በተጨማሪም፥ አንድን ግለሰብ ሳይሆን ሕዝቡን በአጠቃላይ የሚያመለክቱ ናቸው። በረከቶቹም ሆኑ መርገሞቹ ለአንድ ግለሰብ የሚሰነዘሩ ብልጽግናዎች ወይም አደጋዎች አይደሉም። መረጃዎች እንደሚያስረዱት፥ ነቢያት በስምንተኛ፥ ሰባተኛና ስድስተኛው መጀመሪያ ዓ.ዓ. የተናገሩት በአብዛኛው መርገም ነበር። ምክንያቱም ሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት እስከ 722 ዓ.ዓ. ያልተሸነፈ ሲሆን፥ ደቡባዊው የይሁዳ መንግሥትም እስከ 587 ዓ.ዓ. አልወደመም ነበር። እስራኤላውያን (ሰሜንና ደቡብ) በዚያን ጊዜ ወደ ቅጣት እያመሩ ነበር። ስለሆነም እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ንስሐ ለመመለስ በሚያደርገው ጥረት ከበረከት ይልቅ የመርገም ማስጠንቀቂያ በእስራኤላውያን ላይ ሲበዛ እንመለከታለን። የሰሜኑም ሆነ የደቡብ መንግሥት ከተደመሰሰ በኋላ (ከ587 ዓ.ዓ. በኋላ)፥ ነቢያቱ ከመርገም ይልቅ ስለ በረከት ይናገሩ ነበር። ይህም የሆነው ቅጣቱ ከተፈጸመ በኋላ እግዚአብሔር መሠረታዊ ዕቅዱን (ምሕረቱን ማሳየት) በመጀመሩ ነው። (በዘዳግም 4፡25-31 ይህንን ቅደም ተከተል በተመለከተ አጭር ማብራሪያ ታገኛለህ።)

የትንቢት መጻሕፍትን በምታነብበት ጊዜ ይህንን ቀላል የአፈጻጸም ስልት አስተውል። (1) የእስራኤል ኃጢአት ወይም እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለውን ፍቅር ይገልጻል። (2) እንደ ሁኔታው የመርገም ወይም የበረከት ትንበያ። በአብዛኛው መንፈስ ቅዱስ በሰጣቸው መጠን፥ ነቢያት የሚያስተላልፉት መልእክት ይኸው ነው።

ነቢያቱ የሚያስተላልፉት መልእክት ራሳቸው የፈጠሩት ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጣቸው ነው። ነቢያትን ያስነሣቸው እግዚአብሔር ነው (ዘጸ. 3፡ከ1 ጀምሮ፤ ኢሳ. 6፤ ኤር. 1፤ ሕዝ. 1–3፤ ሆሴ. 1፡2፤ አሞጽ 7፡14–15፤ ዮናስ 1፡1፤ ወዘተ… አንብብ)። አንድ ነቢይ በራሱ ሥልጣን ወደ አገልግሎት ከወጣ ይህ ሐሰተኛ ነቢይ ለመሆኑ ጥሩ ማረጋገጫ ነው (ኤር. 14፡14፤ 23፡21)። ነቢያት ለመለኮታዊ ጥሪ ምላሽ የሰጡ አገልጋዮች ናቸው። እንዲያውም ነቢይ የሚለውን ቃል የሚገልጸው የዕብራይስጥ ቃል (ናቢ) «መጥራት» (ናቡ) ከሚለው ሴማዊ ቃል የተገኘ ነው። የአማርኛው ቋንቋ ሐነቢይመን ከዕብራይስጥ እንደ ወረሰ አስተውል ። ነቢያት «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» በሚሉ አገላለጾች በመጠቀም መልእክቶቻቸውን እንደሚጀምሩ፥ እንደሚጨርሱ፥ ወይም ቆም እንደሚያደርጉ ትገነዘባለህ። እንዲያውም ብዙውን ጊዜ ነቢያቱ መልእክቱን ከእግዚአብሔር እንደተቀበሉ በቀጥታ ስለሚናገሩ፥ እግዚአብሔር ራሱ «እኔ» እያለ በአንደኛ መደብ የሚናገርባቸው ጊዜያት አሉ።

ለምሳሌ ያህል፥ ኤርምያስ ምዕራፍ 27ን እና 28ን አንብብ። የይሁዳ ሕዝብ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ከፈለጉ ለጠላት ወታደሮች (ባቢሎናውያን) መገዛት እንደሚገባቸው የሚያስረዳበትን አስቸጋሪ ሥራ አስተውል። ብዙዎቹ አድማጮቹ ይህ መልእክት አገርን ከመካድ እኩል እንደሆነ ማሰባቸው አልቀረም። ይሁንና፥ ይህ የራሱ ሳይሆን የእግዚአብሔር አመለካከት እንደሆነ ግልጽ አድርጎላቸዋል። «እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ--- » (27፡2) በሚሉ ቃላት በመጀመር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያስተላልፋል። «መልእክት ላክ--- » (27፡3)፤ «እንዲህ ብለህ ንገራቸው--- » (27፡4) እና «ይላል እግዚአብሔር» (27፡11) ሲል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያስተላልፋል። ቃሉ የእግዚአብሔር ቃል ነው። የተላለፈውም በራሱ ሳይሆን በእግዚአብሔር ሥልጣን ነው (28፡15–16)።

እግዚአብሔር ለእስራኤልም ሆነ ለሌሎች አገሮች ቃሉን የሚያስተላልፍባቸው መሣሪያዎች እንደ መሆናቸው፥ ነቢያት ማኅበራዊ ሥልጣን ዓይነት ነገር ነበራቸው። ስለሆነም እነዚህ የመለኮታዊ ሉዓላዊውን ፈቃድ ለሕዝቡ እንደሚያደርሱ አምባሳደሮች ነበሩ። ነቢያቱ በራሳቸው አክራሪ የማኅበራዊ ለውጥ አራማጆች ወይም የፈጠራ አሳብ የሚከተሉ ሃይማኖተኞች አልነበሩም። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለማስተላለፍ የፈለጋቸው ማኅበራዊ ተሐድሶዎችና ሃይማኖታዊ አስተሳሰቦች ቀደም ሲል በቃል ኪዳን ሕግ ውስጥ ተካትተው ነበር። እነዚህን ሕግጋት በሚያፈርሱ ወገኖች ላይ የእግዚአብሔር ቃል በነቢያት በኩል ፍርድን ያስከትላል። ቃል ኪዳኑን

ያፈረሱት የቤተ መንግሥት ሰዎች (ለምሳሌ፥ 2ኛ ሳሙ. 12፡1–14፤ 24፡11–17፤ ሆሴዕ 14)፥ ወይም የቤተ ክህነት አገልጋዮች (ሆሴዕ 4፡4–11፤ አሞጽ 7፡17፤ ሚልክ. 2፡1–9)፥ ወይም ሌላ የትኛውም ቡድን ቢሆን፥ ነቢያት ብሔራዊ እርግማን እንደሚመጣ የሚያስገነዝበውን የእግዚአብሔርን መልእክት በታማኝነት ያስተላልፋሉ። እንዲያውም በእግዚአብሔር ቃል ተመርተው ነቢያት ነገሥታትን የሻሩባቸውና የሾሙባቸው ጊዜያትም አሉ (1ኛ ነገ. 19፡16፤ 21፡17–22)። ጦርነት ያወጁባቸው (2ኛ ነገ. 3፡18–19፤ 2ኛ ዜና 20፡14–17፤ ሆሴዕ 5፡5–8) እንዲሁም የጦርነትን መካሄድ የተቃወሙባቸው ጊዜያትም ነበሩ (ኤር. 27፡8–22)።

ስለሆነም፥ በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ የምንመለከተው የእግዚአብሔርን ቃል ነቢዩ እንደተመለከተው ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ነቢዩ ቃሉን እንዲያቀርብ የፈለገበትን መንገድ ጭምር ነው። ነቢዩ፥ ካለ እግዚአብሔር ፈቃድ በግሉ ሊናገር ወይም ሊያደርግ የሚችለው ነገር የለም።

*የነቢዩ ቃል ራሱ ያመነጨው አይደለም።* ነቢያት የቃል ኪዳኑን ማስጠንቀቂያዎች ወይም የተስፋ ቃሎች (ርግማኖችና በረከቶች) ወሳኝ ይዘት ለሕዝቡ እንዲያስተላልፉ እግዚአብሔር መርጧቸዋል። ስለሆነም የነቢያትን ቃላት በምናነብበት ጊዜ የምናነበው ሙሉ በሙሉ አዲስ ሳይሆን፥ በመሠረታዊነት እግዚአብሔር ለሙሴ ከሰጠው ጋር አንድ ዓይነት ነው። ያ መልእክት የተላለፈበት ቅርጽ በከፍተኛ ደረጃ ሊለይ ይችላል። እግዚአብሔር ነቢያቱ የተላኩባቸውን ሰዎች ትኩረት ለማግኘት እንዲችሉ አድርጎ እንዳስነሣቸው ግልጽ ነው። የሰዎችን ትኩረት ማግኘቱ ቀደም ሲል ብዙ ጊዜ የሰሙትን ነገር በራሳቸው አገላለጽ ማቅረብንና እንደገና ማዋቀርን ሊጠይቅ ይችላል። ይህም የተወሰነ ዓይነት «አዲስነት» እንዳለው ያመለክታል። ይህ ግን አዲስን መልእክት ከማስተላለፍ ወይም አሮጌውን መልእክት ከመለወጥ ጋር አንድ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ነቢያትን የመራቸው በፔንታቱክ ቃል ኪዳን ውስጥ የሌለ ዶክትሪን እንዲያስተላልፉ አይደለም። ይህንኑ የመልእክት ጥበቃ የመጀመሪያ ምሳሌ ከሆሴዕ 4፡2 ልትመለከት ትችላለህ፤ «በዚያ ያለው ርግማን፣ መዋሸት፣ መግደል፣ መስረቅና ማመንዘር ብቻ ነው»።

በሆሴዕ ዘመን (ከ750–722 ዓ.ዓ.) እስራኤል ኃጢአት ማብዛቷን በሚገልጸው በዚህ ምንባብ ውስጥ ከአሥርቱ ትእዛዛት አምስቱ ጠቅለል ባለ መልኩ ቀርበዋል። እነዚህም «ርግማን፥» ሦስተኛው ትእዛዝ፥ «የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ» (ዘጸ. 20፡7፤ ዘዳግ. 5፡11)፤ «አትዋሽ» ዘጠነኛው ትእዛዝ፤ «በሐሰት አትመስክር--- » (ዘጸ.

20፡16፤ ዘዳግ. 5፡20)። «መግደል» ስድስተኛው ትእዛዝ፤ «አትግደል» (ዘጸ. 20፡13፤ ዘዳግ. 5፡17)። «መስረቅ» ስምንተኛው ትእዛዝ፤ «አትስረቅ» (ዘጸ. 20፡15፤ ዘዳግ. 5፡18)። «ዝሙት» ሰባተኛው ትእዛዝ፤ «አታመንዝር» (ዘጸ. 20፡14፤ ዘዳግ. 5፡18)።

በመንፈስ ቅዱስ የተመራው ነቢይ የሚያደርገውንና የማያደርገውን ነገር መመልከቱ አስገራሚ ነው። ሆሴዕ አሠርቱን ትእዛዛት ቃል በቃል አይዘረዝርም። ልክ ክርስቶስ በሉቃስ 18፡20 እንደሚያደርገው አጠር አጠር እያደረገ ብቻ ይጠቃቅሳቸዋል። ነገር ግን አምስቱን ብቻ ከተለመደው ቅደም ተከተላቸው ውጭ መጠቃቀሱ ራሱ ለእስራኤላውያን አሥሩንም ትእዛዛት እንዳፈረሱ የሚያመለክት ውጤታማ አሠራር ነበር። አድማጩ አሥሩን ከሰማ በኋላ «ሌሎቹስ? ትክክለኛውስ ቅደም ተከተል? የመጀመሪያው የቃላት አደራደር---» እያለ ማሰቡ አይቀርም ነበር። አድማጮቹ ስለ አሥሩም ትእዛዛት በማስታወስ የቃል ኪዳኑ ሕግ ስለ መሠረታዊ የጽድቅ ደንቦች የሚያስረዳውን ያስተውላሉ። ሆሴዕ ለተመሳሳይ ውጤት አምስቱን ሕግጋት በመጥቀሱ የለወጠው ነገር የለም። ክርስቶስም እንደዚሁ። ነገር ግን ቃል በቃል ከመድገሙ በተሻለ መንገድ ለአድማጮቹ ሕጉን አቅርቦላቸዋል።

ሁለተኛው ምሳሌ መሚሐዊ ትንቢቶችን የሚመለከት ይሆናል። እነዚህስ አዲሶች ናቸው? በፍጹም አይደሉም። በኢሳይያስ 42፥ 49፥ 50 እና 53 ውስጥ በምናገኛቸው መሚሐዊ መዝሙሮቹ ውስጥ ያሉት ዝርዝሮ ጉዳዮች አዲሶች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ስለ መሚሕ የተናገረው ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም። አሳቡ የመነጨው በሕግ ውስጥ ነው። እንደዚያ ባይሆን ክርስቶስ ሕይወቱ በሙሴ፥ በነቢያትና በመዝሙራት የተጻፈው አሳብ ፍጻሜ እንደሆነ እንዴት ሊናገር ይችላል? (ሉቃስ 24፡44)። ስለ መሚሑ አገልግሎት ከሚተነብዩ የሙሴ ሕግ ክፍሎች መካከል ዘዳግም 18፡18 በዋነኛነት የሚታይ ነው፤ እርሱም «ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፤ ቃሌን በአፉ አደርጋለሁ፤ የማዘውንም ሁሉ ይነግራቸዋል።» ይላል።

ዮሐንስ 1፡45 እንደሚያስረዳው፥ ሕግ ቀደም ብሎ ስለ ክርስቶስ ተናግሯል። ስለሆነም ለነቢያት ስለ ክርስቶስ መናገሩ ያን ያህል አዲስ ነገር አልነበረም። በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ትንበያዎቻቸውን ያቀረቡበት ስልትና መጠን ፔንታቱክ ቀደም ብሎ በገለጸው አሳብ መታሰር የለበትም። ነገር ግን በአዲስ «ነቢይ» የሚካሄድ አዲስ ቃል ኪዳን (እንደ ዘዳግም 18 አገላለጽ) የመምጣቱ ጉዳይ ግን የድሮው አሳብ ነው።

## ሐቲታዊ ተግባር

### *የውጫዊ እገዛ አስፈላጊነት*

ያለ ጥናት ወይም ውጫዊ እርዳታ መጽሐፍ ቅዱስ ለሚያነበው ሰው ሁሉ ግልጽ መሆን አለበት የሚለውን የብዙዎች አሳብ በምዕራፍ አንድ ውስጥ ተመልክተናል። የዚህ አሳብ አቅራቢዎች የሚሰጡት ምክንያት፥ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ለእኛ (ለአማኞች) ከጻፈው፥ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ስላለ መጀመሪያ ስናነበው ልንረዳው ይገባል የሚል ነው። እንዲህ ዓይነቱ አመላከከት ግን ትክክል አይደለም። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ከላይ ላይ አይተን የምንገነዘባቸው ሲሆኑ፥ ሌሎቹ ግን አይደሉም። የእግዚአብሔር አሳብ ከሰው አሳብ እንደሚልቅ [መዝ. (92)፡5፤ ኢሳ. 55፡8] ከተገነዘብን፥ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጊዜንና በትዕግሥት ማጥናትን የሚጠይቁ መሆናቸው ሊገርመን አይገባም።

የትንቢት መጻሕፍት እንዲህ ጊዜንና ጥናትን የሚጠይቁ ናቸው። ሰዎች ብዙውን ጊዜ የነቢያትን መጻሕፍት ላይ ላዩን አንብበው ብቻ በአግባቡ የሚገነዘቡ ይመስል በጥልቀት ከማጥናት ይታቀባሉ። ይህ የትምህርት ቤት የመማሪያ መጻሕፍትን ለመጠቀም እንኳ የማይሠራ መንገድ በመሆኑ፥ ለትንቢት መጻሕፍትም እንደ አማራጭ ልንወስደው አይገባም።

እዚህ ላይ በተለይም ትንቢትን ለመተርጎም ስለሚያግዙ ሦስት ዓይነት የእርዳታ ምንጮች መግለጽ ይኖርብናል። የመጀመሪያዎቹ *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት* ናቸው። እነዚህ ምንጮች ስለ መጽሐፉ ታሪካዊ ስፍራ፥ መሠረታዊ አስተዋጽኦ፥ ስለሚይዟቸው ልዩ ገጽታዎችና አንባቢው ሊያውቃቸው ስለሚገቡ የአተረጓጎም ጉዳዮች አሳብ የሚሰጡ ናቸው። አንድ የትንቢት መጽሐፍ ከማንበብህ በፊት በእርሱ ላይ አሳብ የሚሰጡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትን እንድታነብ እንመክርሃለን። ነቢዩ ከሚያስተላልፋቸው አሳቦች ብዙዎቹን ለመያዝ የምትችለው የዳራ መረጃ ስታገኝ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ቃሉን በነቢያት በኩል ያስተላለፈው በተወሰነ ሁኔታ ውስጥ ለነበሩት ሰዎች ነው። መልእክቱን ከሕይወታችን ጋር የምናዛምደው ያንን ሁኔታ የተረዳን እንደሆነ ነው።

ሁለተኞቹ የእርዳታ ምንጮች *መጻሕፍት (commentaries)* ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት ለእያንዳንዱ መጽሐፍ ረዥም መግቢያ ያቀርባሉ። ምንም እንኳ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትን በሚመስል መልኩ ቢቀርቡም፥ ማብራሪያዎች የሚደራጁት ብዙም ጠቃሚ በሆነ መንገድ አይደለም። ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በላይ

ለእያንዳንዱ ጥቅስ ማብራሪያዎችን ይሰጣሉ። እነዚህ ነገሮች መጻሕፍት ከትንቢት መጻሕፍት አነስተኛ ክፍል የምታጠና ከሆነ (በአንድ ጊዜ ከአንድ ምዕራፍ በታች፥ ተጨማሪ አሳቦች የቀረቡባቸውን የመጽሐፉን የመጨረሻ ገጾች ተመልከት) ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል።

ሦስተኛቹ የእርዳታ ምንጮች *የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ (the Bible Handbooks)* ናቸው። ምርጥ የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎች የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትንና የማብራሪያ መጻሕፍትን ይዘቶች ይገልጻሉ። ነገር ግን መግቢያቸውም ሆነ የጥቅስ ማብራሪያቸው በዝርዝር የሚቀርብ አይደለም። ነገር ግን አንድ ሰው ከነቢያት መጻሕፍት ብዙ ክፍል የሚያነብ ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ በአጭር ጊዜ ብዙ ጠቃሚ መመሪያዎችን በመስጠት ሊያገለግለው ይችላል።

## *ታሪካዊ ዓውድ*

ታሪካዊ ዓውድ ክርስቶስ የመጣበትን፥ ሰፊ አካባቢና አንድን ተግባር ያከናወነበትን ወይም አንድን አሳብ የተናገረበትን የተወሰነ ዓውድ እንደሚመለከት ስለ ክርስቶስ ከቀረበው የምዕራፍ 7 ዘገባ የምታስታውሰው ነው። ስለ ነቢያት በምናጠናበት ጊዜም ታሪካዊው ዓውድ ሰፋ ብሎ የራሳቸውን ዘመን ሊሸፍን ወይም ጠበብ ብሎ አንዱን መልእክት ሊያጤን ይችላል። ጥሩ ያኔዚያ ለመሥራት ከፈለግህ የትንቢት መጻሕፍትን ሁለቱንም የታሪካዊ ዓውድ ገጽታዎች መገንዘብ ይኖርብሃል።

*ሰፊው ዓውድ፡—* አሥራ ስድስቱም የትንቢት መጻሕፍት ከረዥሙ የእስራኤል ታሪክ ውስጥ ጥቂቱን ብቻ (ከ760–460 ዓ.ዓ.) የሚሸፍኑ መሆናቸው አስገራሚ ነው። ከአብርሃም ዘመን (1800 ዓ.ዓ. አካባቢ)፥ ከኢያሱ ዘመን (1400 ዓ.ዓ. አካባቢ)፥ ከዳዊት ዘመን (1000 ዓ.ዓ. አካባቢ)፥ የትንቢት መጻሕፍት የሌሉን ለምንድን ነው? ከ760 ዓ.ዓ. በፊት እግዚአብሔር ለሕዝቡና ለዓለማቸው አልተናገረም ማለት ነው? በእርግጥ ተናግሯል። እንዲያውም ስለዚያ ዘመን የሚናገሩ ብዙ ማቴሪያሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ ስለ ነቢያት የተነገሩ ናቸው። (ለምሳሌ፥ 1ኛ ነገ. 17–2ኛ ነገ. 13)። በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር ሕግን፥ በአዲስ ኪዳን እስከተተካው ድረስ ለሕዝቡ ታሪክ ሁሉ እንዲሠራ ባዘጋጀው ሕግ አማካኝነት እንደተናገረ ማስታወሱ ጠቃሚ ነው (ኤር. 31፡31–34)።

ይህ ከሆነ፥ በአሞጽ (760 ዓ.ዓ. አካባቢ፤ መልእክቶቻቸውን በጽሑፍ ካቀዩት መካከል የመጀመሪያው) እና ሚልክያስ (460 አካባቢ፤ የመጨረሻው) መካከል በሚገኙት ሦስት መቶ ዓመታት ውስጥ

የነቢያት መልእክቶች የበረከቱት ለምንድን ነው? ምክንያቱም ይህ ክፍለ ጊዜ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የቃል ኪዳን ማጽኛን ተግባር የሚጠይቅ በመሆኑና ይህም የነቢያት አገልግሎት በመሆኑ ነው። ሁለተኛው ምክንያት በእነዚያ ወሳኝ ዓመታት እግዚአብሔር ነቢያቱ ከእርሱ ተቀብለው ያስተላለፏዋቸውን ማስጠንቀቂያዎችና በረከቶች ለመመዝገብ መፈለጉ ነው።

እነዚያ ዓመታት በሦስት ነገሮች ተለይተው ይታወቃሉ። (1) ታይቶ በማይታወቅ ፖለቲካዊ፥ ወታደራዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ውዝግብ፥ (2) በከፍተኛ ሃይማኖታዊ የታማኝነት ጉድለትና የመጀመሪያውን የሙሴ ቃል ኪዳን ባለማክበር፥ እና (3) የሕዝብ ቁጥርና የብሔራዊ ዳርቻዎች መቀየር ነበር። በእነዚህ ሁኔታዎች ምክንያት እግዚአብሔር ነቢያትን አስነሥቶ ቃሉን በአዲስ መንገድ ለሕዝቡ አስተላልፎአል።

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትን፥ ማብራሪያዎችና የመመሪያ መጻሕፍት በምታነብበት ጊዜ፥ እስራኤል በ760 ዓ.ዓ. አካባቢ ለረዥም ጊዜ በሚቆይ የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት ተከፋፍላ እንደነበር ትገነዘባለህ። «እስራኤል» ወይም አንዳንድ ጊዜ «ኤፍሬም» የሚባሉት ሰሜናዊ ነገዶች ከደቡባዊ የይሁዳ ነገዶች ተለይተው ነበር። በይሁዳ ገና ባልታወቀ መልኩ ቃል ኪዳኑን በከፍተኛ ደረጃ በማፍረስ ላይ የነበሩት የሰሜኑ ነገዶች፥ ከኃጢአታቸው የተነሣ ሊጠፉ ተቃርበው ነበር። አሞጽ ከ765 ዓ.ዓ.፥ ሆሴዕ ደግሞ ከ755 ዓ.ዓ. ጀምሮ እየቀረበ ስለነበረው ጥፋት ይተነብዩ ጀመር። የሰሜኑ መንግሥት በ722 ዓ.ዓ. በወቅቱ በመካከለኛው ምሥራቅ ኃያል አገር በነበረችው በአሦር አገዛዝ ሥር ወደቀ። ከዚያ በኋላ የይሁዳ ኃጢአት እየበዛ በመሄዱና ባቢሎን የተባለች ሌላ ኃያል አገር በመነሣቷ እንደ ኢሳይያስ፥ ኤርምያስ፥ ኢዩኤል፥ ሚክያስ፥ ናሆም፥ ዕንባቆምና ሶፎንያስ የመሳሰሉ ብዙ ነቢያት ለአገልግሎት ተሰማሩ። ይሁዳም ባለመታዘዙ ምክንያት በ587 ዓ.ዓ. ተደመሰሰ። ከዚያ በኋላ ሕዝቅኤል፥ ዳንኤል፥ ሐጌ፥ ዘካርያስና ሚልክያስ ተነሥተው (በ538 ዓ.ዓ. ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ) እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማደስ ስላለው ፈቃድ፥ ስለ አገራቸው ዳግም ግንባታና ስለ ቃል ኪዳናቸው መታደስ አስተማሩ። ይህ ሁሉ በዘዳግም 4፡25-31 የተጣለውን ዋንኛ መሠረት ተከትሎ የሚሄድ ነበር።

ነቢያቱ ለእነዚህ ክስተቶች በቀጥታ ሰፊ መልእክቶችን ያስተላልፉ ነበር። እነዚህንና በዚህ ሰፍራ ለመዘርዘር የሚያስቸግሩትን ሌሎች እጅግ ብዙ ክስተቶች ካላወቅህ ነቢያቱ የሚያስተላልፉትን መልእክት በቅጡ ልትገነዘብ አትችልም። እግዚአብሔር በታሪክ ስለ ታሪክ

እንደተናገረ ግልጽ ነው። በመሆኑም የእርሱን ቃል ለማወቅ ስለዚያ ታሪክ በመጠኑ ግንዛቤ መጨበጥ አለብን።

የውስን ዓውዶች ምሳሌ። እያንዳንዱ ትንቢታዊ መልእክት የተላለፈው በተወሰነ ታሪካዊ ዓውድ ነበር። እግዚአብሔር መልእክቱን ያስተላለፈው በተወሰነ ጊዜ፥ በታና ሁኔታ ውስጥ ለነበሩት ሰዎች ነበር። ስለሆነም ዘመኑን፥ ተደራሲያኑና ሁኔታውን ማወቁ አንባቢው መልእክቱን በትክክል እንዲረዳ በከፍተኛ ደረጃ ያግዘዋል።

በምዕራፉ ውስጥ ከሌሎች መልእክቶች ጋር የተዳበለውንና ዳሩ ግን ራሱን ችሎ የተቀመጠውን የሆሴዕ 5፡8-10 ምንባብ ተመልከት። በዚያን ጊዜ የነበረን ሰው አግኝተህ ብትጠይቅ፥ ይህ የጦርነት መልእክት፥ ማለትም የእግዚአብሔር ፍርድ በጦርነት እንደሚፈጸምበት ዓይነት መሆኑን ይነግርሃል። እንዲህ ዓይነት የመልእክት ቅርጾች የሚዋቀሩት ብዙውን ጊዜ ሕዝብን ለማንቃት፥ ጥቃትን ለመግለጽና ሽንፈትን ለመተንበይ ነበር። ቅርጹን ማወቅ እንደሚያስፈልግ ሁሉ፥ ውስን ይዘቱንም ማወቁ አስፈላጊ ነው።

ጊዜው 734 ዓ.ዓ. ነው። ተደራሲያኑ ሆሴዕ የሚሰብክላቸው የሰሜን እስራኤል ነዋሪዎች (ኤፍሬማውያን) ናቸው። መልእክቱ የተላለፈው በተለይ ከየይሁዳ መዲና ከሆነችው ኢየሩሳሌም እስከ የእስራኤል የሐሰተኛ አምልኮ ማዕከል እስከሆነችው ቤቴል ድረስ ላሉት ከተሞች ነበር። ሁኔታው ጦርነት ነበር። እስራኤልና አሦር ይሁዳን ከወረሯት በኋላ ይሁዳ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ ወስዳ ነበር (2ኛ ነገ. 16፡5 አንብብ)። ነገር ግን የወቅቱ ኃያል አገር የሆነችው አሦር እገዛ በማድረጓ እስራኤል መልሳ ልታጠቃት ቻለች (2ኛ ነገ. 16፡6-9)። እግዚአብሔር በብንያም ግዛት ውስጥ ለሚገኙ (ቁ.8) እና የሰሜኑ መንግሥት አካላት ለሆኑት ከተሞች በሆሴዕ በኩል ፈሊጣዊ መልእክት ያስተላልፋል። ይሁዳ የወረረችውን ግዛት ስለምትይዝ («የወሰን ድንጋዮችን እንደሚነቅሉ ሰዎች») ውድመቱ የማይቀር ይሆናል (ቁ.9)። ይሁዳም ግን በተራዋ ትወድማለች። ለዚህ የጦርነት ተግባርና ለጣዖት አምላኪነታቸው የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱም ላይ ይወርዳል (2ኛ ነገ. 16፡2-4 አንብብ)። ይሁዳና እስራኤል እንዲህ ዓይነቱን አውዳሚ ጦርነት በሚከለክል ቃል ኪዳን ሥር ነበሩ። ስለሆነም እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ስላፈረሱ ይቀጣቸዋል።

እነዚህን አነስተኛ መረጃዎች ማወቁ በሆሴዕ 5፡8-10 ላይ ለሚኖረን ግንዛቤ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል። የነቢያትን መጻሕፍት በምታነብበት ጊዜ ማብራሪያዎችን ወይም የመመሪያ መጻሕፍትን

በማጣቀሻነት ተጠቀም። እንዲሁም ደግሞ የምታነባቸውን መልእክቶች ዘመን፥ ተደራሲያንና ሁኔታ ለማወቅ ጣር።

*መልእክቶችን ለብቻ መነጠል*

አንድ ሰው የነቢያት መጻሕፍትን በአግባቡ ለማጥናት ወይም በሐቲታዊ መንገድ ለማንበብ በሚፈልግበት ጊዜ የመጀመሪያ ተግባሩ ውስን መልእክቶችን (oracles) ማሰብ ይሆናል። (ይህም ቀደም ሲል ለአዲስ ኪዳን መልእክቶች አንቀጾችን ማሰብ እንደሚገባ የገለጽነው ዓይነት ነው።) ይህ ሁልጊዜ ቀላል ተግባር አይደለም። ነገር ግን ችግሩንና ይህንኑ የማድረጉን አስፈላጊነት መገንዘቡ የአሰደሳች ግኝት ጅማሬ ነው።

በአብዛኛው ነቢያት ያስተላለፉዋቸው መልእክቶች በምዕራፍ ሳይከፋፈሉ አንድ ላይ ነበር። ስለሆነም በተለያዩ ጊዜያትና ስፍራዎች ያቀረቧቸው መልእክቶች አንዱ የሚያበቃበትና ሌላው የሚጀምርበት ቦታ ሳይታወቅ በአንድ ላይ ሰፍረው እናገኛለን። በተጨማሪም፥ ከፍተኛ የርእስ ጉዳይ ለውጥ ከመከሰቱ የተነሣ አዲሱ መልእክት የጀመረበትን ለማወቅ ቢቻልም እንኳ፥ ከትንቢት መጽሐፉ ማብራሪያ ማግኘት ስለማይቻል የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለማንሣት የምንገደድባቸው ሁኔታዎች አሉ። «ይህ የተነገረው በተመሳሳይ ቀን ለተመሳሳይ ተደራሲያን ነው ወይስ ከዓመታት በኋላ ወይም በፊት ነው? በተለየ ሁኔታ ውስጥ ለነበሩት ሌሎች ሰዎች ይሆን?» ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ አንድ ሰው ከመልእክቱ የሚያገኘውን አሳብ በእጅጉ ይለውጠዋል።

አንዳንድ የነቢያት መጻሕፍት ክፍሎች የተለዩ ሁኔታዎችን ያቀርባሉ። ለምሳሌ፥ በሐጌና በዘካርያስ እያንዳንዱ ትንቢት ቀን ተጽፎለታል። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፥ በመመሪያ መጽሐፍ ወይም በማብራሪያ መጽሐፍ በመጠቀም የትንቢቶቹን ታሪካዊ ዓውድ በቀላሉ ልትለይ ትችላለህ። በሌሎች መጻሕፍትም በተለይም በሕዝቅኤልና በኤርምያስ ውስጥ አንዳንድ ትንቢቶች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በጻፉት ደራሲያን ቀን ተሰጥቷቸው በዓውዳቸው ቀርበዋል።

ይህ ግን ብዙውን ጊዜ የሚታይ ነገር አይደለም። ለምሳሌ፥ እስኪ አሞጽ ምዕራፍ 5ን የማብራሪያ ርእሶችን (እነዚህ ርእሶች የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ያቀረቧቸው አሳቦች ናቸው) ከማይሰጥ መጽሐፍ ቅዱስ አንብብና ጠቅላላው ምዕራፍ አንድ መልእክት ነው ወይስ አይደለም? ብለህ ጠይቅ። አንድ መልእክት ከሆነ፥ ርእሰ ጉዳዮቹን የሚቀያይረው ለምንድን ነው? (በእስራኤል ውድመት ላይ ለቅሶ፥ ቁ. 1-3፤ እግዚአብሔርን እንዲፈልጉና በሕይወት እንዲኖሩ የቀረበ ግብዣ፥ ቁ.

5–6፥ 14፤ የማኅበራዊ ፍትሕ አልበኝነት ተቃውሞ፥ ቁ. 7–13፤ ችግሮች እንደሚመጡ የሚያስረዳ ትንቢት፥ ቁ. 16–17፥ ስለ ጌታ ቀን የተሰጠ ገለጻ፥ 18–20፤ የማብዝነት አምልኮ ትችት፥ ቁ. 21–24፤ በኃጢአት የተሞላ የእስራኤል ታሪክ ክለሳና ምርኮ፥ ቁ. 25–27)። አንድ መልእክት ከሆነ እነዚህን ተያያዥ ክፍሎች እንዴት መረዳት ይቻላል? አንዱ በሌላው ላይ አይደገፍም? አንዳንዶቹ በአንድ ቡድን ሊቀመጡ የሚችሉ ናቸው? እንደዚያ ከሆነስ እንዴት?

በምዕራፍ 5 ውስጥ የምናገኘው ሦስት መልእክቶች እንደሆኑ የሚታመኑትን አሳቦች ነው። ከቁጥር 1–3 ቅጣት እንደሚመጣ የሚያመለክት አንድ አጭር የሰቆቃ መልእክት ቀርቧል። ከቁጥር 4–17 ሕዝቡ ወደ በረከት እንዲመጡና ካልሆነም ቅጣት እንደሚጠብቃቸው የሚያስጠነቅቅ አንድ ውስብስብ መልእክት ይዞአል። ከ18–27 ስለ ቅጣት የሚያስጠነቅቅ አንድ ውስብስብ መልእክት ያቀርባል። ስለሆነም የርእስ ጉዳዮች በትንሹ መለወጥ የአዲስ መልእክትን ጅማሬ አያመለክትም ማለት ነው። በሌላ በኩል፥ የምዕራፍ አከፋፈሎቹም ቢሆኑ እያንዳንዱን መልእክት የሚይዙ አይደሉም። የትንቢት መልእክቶች የሚለዩት ከሚቀርቡበት ቅርጽ ነው። (ከታች የቀረበውን አሳብ አንብብ።) እነዚህ ሦስቱም መልእክቶች የተሰጡት በኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት መጨረሻ አካባቢ (793–753 ዓ.ዓ.) ነበር። እነዚህ ትንቢታዊ መልእክቶች የተሰጡት ከመጠነኛ ብልጽግናቸው የተነሣ አገራቸው በአንድ ትውልድ ዘመን እንደምትጠፋ የሚያስረዳውን አሳብ ለመቀበል ለተቸገሩት ሰዎች ነበር። ጥሩ ማብራሪያ፥ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ወይም መመሪያ መጽሐፍ እነዚህን ነገሮች ያብራሩልሃል። በእነዚህ በአንዳቸው ሳትጠቀም ለማጥናት እየሞከርህ ራስህን አታስጨንቅ።

## *የትንቢት ማቅረቢያ ቅርጾች*

አንዱን መልእክት ነጥሎ ማየቱ የትንቢት መጻሕፍትን ለመረዳት ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ፥ ነቢያት መልእክቶቻቸውን ለማዘጋጀት የሚጠቀሙባቸውን የተለያዩ ቅርጾች ማወቁ ጠቃሚ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከተለያዩ ሥነ ጽሑፎችና ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾች እንደተዋቀሩ ሁሉ፥ ነቢያትም በመለኮታዊ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ያገኙዋቸውን መልእክቶች ለማስተላለፍ የተለያዩ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾችን ተጠቅመዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎች እነዚህን ቅርጾች ያብራሩልሃል። በእኛ በኩል፥ በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን ሥነ ጽሑፋዊ ቴክኒኮች መለየትና በአግባቡ መተርጎም ምን ያህል

ጠቃሚ እንደሆነ እንድትገነዘብ ሦስት በጣም የተለመዱትን ቅርጾች መርጠናል።

*የሕግ ችሎት፦* መጀመሪያ «የቃል ኪዳን የሕግ ችሎት» (በዕብራይስጥ ሪብ) ለሚባለው ስውር የመልእክት ማስተላለፊያ (አሌጎሪ) ቅርጽ መሠረት የሆነውን ኢሳይያስ 3፥13–26 እንድታነብ እንመክርሃለን። በዚህና በሌሎችም የሕግ ችሎት ቅርጾች ውስጥ (ለምሳሌ፥ ሆሴዕ 3፥3–17፤ 4፥1–19፤ ወዘተ...) እግዚአብሔር እንደ ዐቃቤ ሕግ፥ ዳኛና ሕግ አስፈጻሚ በመሆን ተከሳሿን እስራኤልን ሲሞግት እንመለከታለን። ሙሉው የሕግ ችሎት ቅርጽ መጥሪያን፥ ክስን፥ መረጃንና ብያኔን የሚያካትት ሲሆን፥ እነዚህ አላባውያን አንዳንድ ጊዜ በቀጥታ ሳይሆን በአንድምታዊ መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። በኢሳይያስ 3 አላባውያኑ የተቀናጁት በሚከተለው መንገድ ነው። ችሎቱ ተሰባስቦ በእስራኤል ላይ ክስ ያቀርባል (ቁ. 13–14)። ክሱ በንባብ ይሰማል (ቁ. 14–16)። እስራኤል በግልጽ ጥፋተኛ መሆኗን መረጃ ስለሚያሳይ የፍርድ ብያኔ ይሰጣል (ቁ. 17–26)። ቃል ኪዳኑን ስላፈረሱት በቃል ኪዳኑ ውስጥ የሰፈሩት ቅጣቶች በእስራኤል ሴቶችና ወንዶች ላይ ይፈጸማሉ። እነዚህም በሽታ፥ ጥፋት፥ እጦትና ሞት ናቸው። ይህ ልዩ መልእክት የሚተላለፍበት መንገድ እስራኤል ለጥፋቷ እንደምትቀጣና ቅጣቱም የከፋ እንደሚሆን የሚያመለክት ነው። ይህ ልዩ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ልዩውን መልእክት ለማስተላለፍ ያገለግላል።

*ዋይታ፦* ሌላው የተለመደ ቅርጽ «የዋይታ መልእክት» ነው። ዋይታ የጥንት እስራኤላውያን አደጋ፥ ሞት በሚያጋጥማቸው ጊዜ የሚያሰሙት የጩኸት ድምፅ ነበር። እግዚአብሔር ይህንኑ ቃል በመጠቀም በነቢያቱ አማካኝነት ስለሚመጣባቸው አስከፊ ሁኔታ ተንብዮላቸዋል። መልእክቱ ደግሞ ከማንኛውም የተሰወረ አልነበረም። የዋይታ መልእክቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚይዟቸው ሦስት መለያዎች አሏቸው። እነዚህም የመከራ እወጃ (ለምሳሌ «ወየው» የሚለው ቃል)፥ የመከራው ምክንያትና የጥፋት ትንበያዎች ናቸው። በትንቢተ ዕንባቆም ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች ከቀረቡት የዋይታ መልእክቶች አንዱ በባቢሎን ላይ የተነገረው ነው። ይህንንም ከ2፥6–8 ልትመለከት ትችላለህ። በጥንቷ ለምለም አገር ውስጥ የነበረችው ጨካኟና ኢምፔሪያሊስቷ ባቢሎን በሰባተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ይሁዳን ለመውረር እያቀደች ነበር። ዕንባቆምም የተቃውሞ ትንቢት የተናገረው በዚሁ ጊዜ ነበር። ባቢሎንን በሌባና ቀማኛ በመምሰል ትንቢታዊው መልእክት ዋይታን ያስተጋባል፤ የመከራን መምጣት ይተነብያል (አንድ ቀን ባቢሎን የጨቆነቻቸው ሁሉ

እንደሚነሡባት ያመለክታል)። ምንም እንኳ ሁሉም የዋይታ መልእክቶች ስውር ምሥጢር አዘል ባይሆኑም (ሚክ. 2፡1-5፤ ሶፎ. 2፡5-7 ተመለከት)፥ በባቢሎን ላይ የተነገረው የዋይታ ትንቢት ስውር ምሥጢር አዘል ነው።

*የተስፋ ቃል።* ሌላው የተለመደ የትንቢት ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ የተስፋ ቃል ወይም «የደኅንነት መልእክት» ነው። ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች፥ ስለ ሥር ነቀል ለውጦችና ስለ በረከት የሚናገሩ አላባውያን የዚህ ትንቢታዊ ቅርጽ አመልካቾች ናቸው። ሁነኛ የተስፋ ቃል ትንቢታዊ መልእክት የሆነው አሞጽ 9፡11-15 እነዚህን አላባውያን ያካትታል። «በዚያን ቀን» የሚለው ሐረግ ወደፊት የሚሆነውን ያመለክታል (ቁ. 11)። የዳዊት የወደቀው ድንኳ እንደሚመለስ (ቁ. 11)፥ እስራኤል በኤዶም ላይ ከፍ ከፍ እንደምትል (ቁ. 12) እና የእስራኤል ከምርኮ መመለስ (ቁ. 14-15) ታላቅ ሥር ነቀል ለውጥ እንደሚከሰት ያመለክታሉ። በረከት የሚመጣው በተጠቀሱት የቃል ኪዳን ምድቦች አማካኝነት ይሆናል (ሕይወት፥ ጤንነት፥ ብልጽግና፥ የእርሻ መትረፍረፍ፥ አክብሮትና ደኅንነት)። ምንም እንኳ ጤንነት በቀጥታ ባይገለጽም፥ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በአሞጽ 9፡11-15 ተካትተዋል። ዋንኛ ትኩረት የተሰጠው ለእርሻ ነው። ለምሳሌ፥ እህል በጣም ስለሚበዛ የመዝራት ዘመን እስከሚጀመር ድረስ የበፊቱን ሰብስቦ መጨረስ ሳይቻል ይቀራል! (ቁ. 13)። ሌሎች የተስፋ ቃል ትንቢታዊ መልእክቶችን ከሆሴዕ 2፡16-20፤ 2፡21-23፤ ኢሳ. 45፡1-7 እና ከኤርምያስ 31፡1-9 አንብብ።

ከእነዚህ አጫጭር ምሳሌዎች ትንቢታዊ ሥነ ጽሑፋዊ መማሪያዎችን ማወቁ የእግዚአብሔርን ቃል ይበልጥ በትክክል እንድትገነዘብ የሚያግዝህ መሆኑን እንደተረዳህ ተስፋ እናደርጋለን። የማብራሪያ መጻሕፍትን በማንበብ ትንቢታዊ ቅርጾችን ልትረዳ ትችላለህ (ተጨማሪ አሳቦች የቀረቡባቸውን የመጨረሻ ገጾች ተመልከት)። ይህንን በማድረግህም ደስተኛ እንደምትሆንም አትጠራጠር።

## *ነቢያት እንደ ገጣሚያን*

በተለይ በአሜሪካ ብዙ ሰው ለግጥም ከፍተኛ ትኩረት አይሰጥም። ለእነዚህ ወገኖች ግጥም አሳብን ለመግለጽ ግራ የሚያጋባና እንግዳ መንገድ ይመስላቸዋል። አሳቦችን ፍንትው አድርጎ ከማውጣት ይልቅ ወደ ማድበስበሱ የሚያዘነብል ይመስላል። ከተራ የዘፈን ግጥም በስተቀር ማኅበረሰቡ ለግጥም ብዙም ትኩረት አይሰጥም። ነገር ግን በአሁኖቹ አንዳንድ ባሕሎችና በድሮዎቹ ባሕሎች ውስጥ በአመዛኙ

ግጥም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የአገላለጽ መንገድ ነበር። አጠቃላይ ብሔራዊ ታሪኮችና ቁልፍ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ መታሰቢያዎች ለመጭዎቹ ትውልዶች ተጠብቀው እንዲቆዩ የተደረገው በግጥም ነው። «ተጠብቀው ቆዩ» የምንለው ከዝርው ጽሑፍ ይልቅ ግጥም ሳይረሳ በቃል የመተላለፍ ብቃት ስላለው ነው። ግጥም እንደ ምሪት (ሪትም እና ሜትር)፥ ትይዩነት (ፓራሌሊዝም ወይም ስቲኮሜትሪ) የመሳሰሉ መዋቅሮች አሉት። ይህም በአንጻራዊ መልኩ መደበኛና ሥርዓታዊ ነው። ጥሩ አድርገው ከተማሩት ግጥም እንደ ዝርው ንባብ በቀላሉ የሚረሳ አይደለም።

ነቢያት አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙበት ግጥማዊ ዝርው ጽሑፍ መደበኛነት ባይታይበትም እነዚሁ ባሕርያት የሚንጸባረቁበት ነው። ከተራ የንግግር ቃላት በላይ መደበኛና ስልታዊ በመሆኑ የበለጠ የመታወስ ብቃት አለው።

በጥንቷ እስራኤል ግጥም እንደ መማሪያ መንገድ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠው ነበር። ሊታወሱ ይገባል የሚባሉ ብዙ ነገሮች በግጥም ይጻፉ ነበር። እኛ ከመጻሕፍት ወይም ንግግሮችን ዓረፍተ ነገሮችን ከማስታወስ ይልቅ የመዝሙር ግጥሞችን በቀላሉ እንደምናስታውስ ሁሉ፥ እስራኤላውያንም ግጥም አጥንቶ ማስታወሱን እንደ ጥሩ አማራጭ ወስደው ነበር። ብዙዎች ማንበብና መጻፍ በማይችሉበትና በግላቸው መጽሐፍ ሊጠቀሙ በማይችሉበት ዘመን እግዚአብሔር ይህንን ጠቃሚ መማሪያ በመጠቀም በነቢያቱ በኩል ተናግሯል። ሰዎቹ ግጥም በቃላቸው የመያዝ ልምድ ስለነበራቸው ለረዥም ጊዜ ያስታውሷቸው ነበር። እነዚህ ግጥሞች ጆሮዎቻቸው ላይ ያቃጭሉባቸዋል።

የትንቢት መጻሕፍት ሁሉ ብዙ ግጥሞችን የሚያካትቱ ሲሆኑ፥ አንዳንዶቹ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ በግጥም የቀረቡ ናቸው። ስለሆነም ትንቢታዊ መጻሕፍትን ከማንበብህ በፊት የዕብራውያንን የግጥም ስልት ማወቁ ሊጠቅምህ ይችላል። በተለይም በInterpreter's Dictionary of the Bible (Nashville: Abingdon, 1962) ውስጥ ኖርማን ጎትዎልድ ሙጽሮ ትርይ፥ ሕ ብር ውሚ በሚል ርእስ የጻፉትን ማንበቡ ጠቃሚ ይሆናል። ነገር ግን የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ስለ ግጥም የተወሰነ መልእክት እንደሚያስተላልፍ ግልጽ ነው። የዕብራይስጥ የግጥም ስልት ምን እንደሚመስል ለመረዳት በብሉይ ኪዳን ግጥም ውስጥ ተደጋግመው የሚታዩትን ቀጣይ ሦስት ገጽታዎች መመልከቱ ጠቃሚ ነው።

1. *ተመሳሳይ ትይዩነት* (Synonymous parallelism)* በኢሳይያስ 44፡22 እንደተመለከተው፥ ሁለተኛው ስንኝ የመጀመሪያውን አሳብ ያጠናክረዋል ወይም ይደግመዋል።

«መተላለፍህን እንደ ደመና፥

ኀጢአትህን እንደ ማለዳ ጭጋግ ጠርጌ አስወግጃለሁ።»

2. *ተቃርኖአዊ ትይዩነት* (Anthithetical parallelism) )* በሆሴዕ 7፡14 እንደተመለከተው ሁለተኛው ስንኝ የመጀመሪያውን ይቃረነዋል።

«ከልባቸው ወደ እኔ አይጮኹም፤

ነገር ግን በአልጋቸው ሆነው ያለቅሳሉ።»

3. ተጨማሪ ትይዩነት (Synthetic paralelsim)። በአብድዩ 21 ላይ እንደተመለከተው፥ ሁለተኛው ስንኝ ለመጀመሪያው ስንኝ ተጨማሪ አሳቦችን ይሰጣል።

«የዔሳውን ተራሮች ለመግዛት፣

ነፃ አውጪዎች ወደ ጽዮን ተራራ ይወጣሉ፤

መንግሥቱም የእግዚአብሔር ይሆናል።»

በጥንቃቄና በማስተዋል እስካነበብህ ድረስ አሳቦች በግጥም መልክ መቅረባቸው ሊያደናግርህ አይገባም። ደንቦቹን ካወቅህ ግጥምን እንደ ዝርው ንባብ ልትረዳው ትችላለህ።

## አንዳንድ ሥነ አፈታታዊ አሳቦች

የሐቲት ተግባር ነቢያትን በራሳቸው ታሪካዊ ዓውዶች ውስጥ ማስቀመጥና እግዚአብሔር በእነርሱ አማካኝነት ለእስራኤል የተናገረውን አሳብ መስማት ከሆነ፥ በሥነ አፈታታዊ ደረጃስ ምን ልንል እንችላለን? በሌላ ጊዜ ለጥንታዊ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የተነገሩት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተላለፉ ግጥማዊ መልእክቶች ለእኛስ ምን የሚሉት አላቸው? በመጀመሪያ፥ በምዕራፍ 4 ስለ መልእክቶች የተነገረው በአብዛኛው እዚህም ላይ እንደሚሠራ ለመግለጽ እንፈልጋለን። እግዚአብሔር ለእነርሱ ያስተላለፈውን መልእክት ከሰማን ወዲያ በራሳችንም ሁኔታ በቀጥተኛ መንገድ መስማታችን የማይቀር ነው። አሁንም ቢሆን ችግረኛውን ስለ ጥንድ ጫማ በሚሸጡት (አሞጽ 2፡6)፥ ሃይማኖትን የስግብግብነትና የፍትሕ አልበኝነት መሸፋፈኛ በሚያደርጉት (ኢሳ. 1፡10–17)፥ ዘመናዊ ጣዖት

አምላኪነትን (ራስን እንደማጽደቅ ያለ) ከክርስቶስ ወንጌል ጋር በሚቀይጡት ላይ (ሆሴዕ 13፡2–4) የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚመጣ እናምናለን። እነዚህ ኃጢአቶች በአዲሱ ቃል ኪዳን ውስጥም ኃጢአቶች ናቸው። እነዚህ አሮጌውም ሆነ አዲሱ ኪዳን የሚጋሯቸውን ሁለት ታላላቅ ትእዛዛት ይጥሳሉ (ምዕራፍ 9ን ተመልከት)።

ከዚህ ዓይነቱ ተዛምዶ ባሻገር ሊዳሰሱ የሚገባቸው ሦስት ተጨማሪ አካባቢዎች አሉ። እነዚህም የማስጠንቀቂያ፥ የስጋትና የጥቅም አካባቢዎች ናቸው።

*ማስጠንቀቂያ፡ ነቢይ ወደፊት የሚሆነውን አመልካች*

ወደፊት ከረዥም ጊዜ በኋላ የሚሆነውን መተንበይ የነቢያት ቀዳማይ ተግባር እንዳልሆነ በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ አካባቢ ገልጸናል። ነቢያቱ ወደፊት የሚሆኑትን ነገሮች የተነበዩ ቢሆንም፥ ያ ገና አሁን ለእኛ በአብዛኛው ያለፈ ክስተት ነው። ይህም ማለት ስለ መጭው ፍርድ ወይም ደኅንነት የተነበዩት በአንጻራዊ መልኩ ከእስራኤል የቅርብ ጊዜ ገጠመኝ አኳያ እንጂ ስለ እኛ የወደፊት ሕይወት በማሰብ አይደለም። ለእነርሱ ገና የወደፊት ክስተቶች ሆነው ሳሉ እኛ ግን ዘወር ብለን ስንመለከት የተፈጸሙት ትንቢቶች ከኋላችን እንደቀሩ መገንዘብ ይኖርብናል። ይህንን ሥነ አፈታታዊ መርህ በግልጽ ለማብራራት ምሳሌ መጠቀም ይኖርብናል።

የነቢያት መልእክት በቅርብ ርቀት የሚገኙትን እንጂ በጣም ርቀው ያሉትን ጉዳዮች እንደማይመለከት ለመገንዘብ ሕዝቅኤል 25–39ን አንብብ። በዚያ ሰፊ ክፍል ውስጥ የቀረቡት የተለያዩ መልእክቶች በአብዛኛው ከእስራኤል ውጭ ስላሉት አገሮች ዕጣ ፈንታ የሚናገሩ መሆናቸውን አስተውል። ምንም እንኳ እስራኤልም ከዝርዝሩ ውስጥ የተካተተች ብትሆንም። እግዚአብሔር የተናገረው ስለ እነዚያ አገሮች ዕጣ ፈንታ መሆኑንና ትንቢቱም በተነገረ በአሥርተ ዓመታት ውስጥ እንደተፈጸመ መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። ይህም ማለት ትንቢቶቹ በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን (ዓ.ዓ.) ተፈጽመዋል ማለት ነው። ከዚህ ወጣ የሚሉ ትንቢቶች እንዳሉም ግልጽ ነው። ሕዝቅኤል 37፡15–28 ስለ አዲሱ ኪዳን ዘመንና እግዚአብሔር በመሢሑ አማካኝነት በቤተ ክርስቲያን ላይ ስለሚያፈሳቸው በረከቶች ይናገራል። ነገር ግን አብዛኞቹ ትንቢቶች ምዕራፍ 38ንና 39ን (የእነዚህን ምዕራፎች አሳብ ለመረዳት የማብራሪያ መጻሕፍትን አንብብ) ጨምሮ የብሉይ ኪዳንን ዘመንና ክስተቶች የሚመለከቱ ናቸው።


የአዲስ ኪዳን ክስተቶችን በብሉይ ኪዳን ትንቢታዊ መልእክቶች ውስጥ ለማግኘት የሚደረግ ከፍተኛ ቅንዓት እንግዳ የሆኑ ውጤቶችን

ሊያስከትል ይችላል። በኢሳይያስ 49፡23 ነገሥታት «በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዱልሻል» የሚለው ክርስቶስን የጎበኙት ሰብዓ ሰገል ያደረጉትን ተግባር የሚያመለክት ይመስላል (ማቴ. 2፡1–11)። ይህም ብዙዎች የኢሳይያስ መልእክት መሢሐዊ ነው ብለው እንዲያስቡ አድርጓቸዋል። የሚያሳዝነው እንዲህ ዓይነቱ አተረጓጎም ዓውደ ንባቡን (ነገሥታትና ንግሥታት ሁለቱም ተጠቅሰዋል፤ ምንባቡ የሚያነሣው አሳብ እስራኤል በባቢሎን ከተማረከች በኋላ ስለምትታደስበት ሁኔታ ነው) *ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት* (የመልእክቱ የቋንቋ ቃና እግዚአብሔር ወደ ቀድሞ ክብሯ በመለሳት ጊዜ የእስራኤል ክብር ምን ያህል ከፍ እንደሚል ለማሳየት ይፈልጋል)፥ *የጸሐፊን ስልት* (ግጥሙ የአሕዛብ ነገሥታት ለእስራኤል አሳዳጊ አባቶች እንደሚሆኑና የእግሯን ትቢያ እንደሚልሱ በሚገልጹ ተምሳሌታዊ ቃላት እስራኤል የምታገኘውን ክብር ያጎላል) እና *የቃላት አጠቃቀም* (ሰብዓ ሰገል ኮከብ ቆጣሪዎች እንጂ ነገሥታት አይደሉም) ያላገናዘበ ነው። ትንቢታዊ መልእክቶችም ሆኑ የትኞቹም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እኛ የምንፈልገውን እንዲሉ ከመጣር መቆጠብ ይኖርብናል። እግዚአብሔር ለማስተላለፍ የሚፈልገውን መስማት አለብን።


በቅርብ ርቀት የሚፈጸሙ አንዳንድ ትንቢቶች ከታላቁ የፍጻሜ ዘመን ( ስችህ ትዥልዥግ ች ል ፍኍትኍር ) አንጻር የተነገሩ መሆናቸውንና አንዳንድ ጊዜ ሁለቱ የተጣመሩ እንደሚመስል መገንዘቡ ተገቢ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ በምዕራፍ 13 ውስጥ ሰፊ አሳብ የምናቀርብ ሲሆን፥ ለጊዜው ግን ለዚህ ምክንያቱ ምን እንደሆነ እንገልጻለን። ምክንያቱ እግዚአብሔር በአንድ የታሪክ ወቅት የሚያደርገውን ተግባር መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ልጆች በሙሉ ካለው አጠቃላይ ዕቅድ አንጻር የሚመለከት መሆኑ ነው። ስለሆነም ጊዜያዊው ከዘላለማዊ ዕቅድ አንጻር መታየት አለበት። ይህ ትንሽ ዲስክ ከትልቁ ፊት ቆሞ እንደመመልከት ዓይነት ነው። ከዚያም ከቀጣዩ ታሪክ ከጎን መመልከትና በመካከላቸው ምን ያህል ርቀት እንዳለ ማወቅ።

## የቅደም ተከተላዊ ክስተቶች ትንቢታዊ እይታ

የፊት ለፊት እይታ



የጎን እይታ



በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ ስለ መጨረሻው ዘመን የሚናገሩ ክፍሎችም አሉ (ኢዩ. 3፡1–3፤ ሶፎ. 3፡8–9፤ ዘካ. 14፡9)። ነገር ግን ከእነዚህ የመጨረሻ ዘመን ጉዳዮች ጋር ተያይዘው የቀረቡት ጊዜያዊ ፍርዶችም ወደ መጨረሻው ዘመን ሊገፉ አይገባም።

ሌላው ሊጠቀስ የሚገባው ተጨማሪ አሳብ የመጨረሻው ዘመን ቋንቋ በባሕርዩ ብዙውን ጊዜ ዘይቤያዊ መሆኑ ነው። አንዳንድ ጊዜ እነዚያ ዘይቤያዊ አገላለጾች የመጨረሻውን ዘመን ክስተቶች በቅኔያዊ ቋንቋ የሚናገሩ ቢሆኑም፥ ነገር ግን የግድ የእነዚያ ክስተቶች ትንበያዎች አለመሆናቸውን ማስተዋሉ ጠቃሚ ነው። ለዚህ የሚሆን ምሳሌ ከሕዝቅኤል 37፡1–14 መመልከት ይቻላል። እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን የሚፈጸመውን የሙታን ትንሣኤ ቋንቋ በመጠቀም፥ እስራኤላውያን ከባቢሎን ምርኮአቸው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን (ዓ.ዓ.) ነፃ እንደሚወጡና ወደ አገራቸው እንደሚመለሱ በሕዝቅኤል በኩል ተንብዮአል (ቁ. 12–14)። ስለሆነም ይህ ለእኛ ኃላፊ ጊዜ የሆነው ክስተት (በዕዝራ 1–2 እንደተገለጸው) የመጨረሻው ዘመን ክስተት እንደሚሆን በሚያሳዩ ቃላት በዘይቤያዊ አገላለጽ ተተንብዮአል።

*ስጋት፡- ትንቢትና ሁለተኛ ፍችዎች*

በአያሌ ስፍራዎች አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ምንባቦችን ይጠቅሳል። እነዚህም አዲስ ኪዳን የሚለውን መልእክት የሚያስተላልፉ አይመስሉም። ይህም እነዚህ ምንባቦች በመጀመሪያው የብሉይ ኪዳን ዓውዳቸው ተገቢ ትርጉም ያላቸው ሲመስሉ፥ የአዲስ ኪዳን ደራሲያን ደግሞ ከሌላ ትርጉም አያይዘው ማቅረባቸው ነው።

ለአብነት ያህል፥ ሙሴና እስራኤላውያን በምድረ በዳ እንዴት ውኃ ከዓለት አግኝተው እንደጠጡ የሚያስረዱትን ሁለት ታሪኮች ተመልከት። ይህም አንድ ጊዜ በራፊዲም (ዘጸ. 17፡1–7)፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ በቃዴስ የተከናወነ ተግባር ነበር (ዘኁል. 20፡1–13)። እነዚህ ታሪኮች በመጀመሪያዎቹ ዓውዶቻቸው በጣም ግልጽ ይመስላሉ። ነገር ግን በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡4 ጳውሎስ የእስራኤላውያኑ ገጠመኝ ከክርስቶስ ጋር የተገናኙበት እንደሆነ ያስረዳል። «--- ይከተላቸው ከነበረው መንፈሳዊ ዐለት ጠጥተዋልና፤ ያ ዐለት ክርስቶስ ነበረ» ይላል። በብሉይ ኪዳን ታሪክ ዓለቱ ዓለት ብቻ እንጂ ሌላ ነገር መሆኑ አልተመለከተም ነበር። ጳውሎስ ለዓለቱ ሁለተኛ ፍች በመስጠት ክርስቶስ መሆኑን ይነግረናል። ይህ ሁለተኛ ፍች በተለምዶ «ሙሉ ፍች» ተብሎ ይታወቃል።

ክፍሉን አስተውለን ከተመለከትን፥ ጳውሎስ ምስያ እየተጠቀመ መሆኑን እንገነዘባለን። ይህም፥ «ያ ክርስቶስ ለእኛ እንደሆነው ያ ዓለት ለእነርሱ ነበር፤ ለእነርሱ ቁሳዊ ነገሮች ድጋፍ እንደሆኑላቸው ለእኛም ክርስቶስ መንፈሳዊ ድጋፋችን ነው» የሚል አንድምታ ያለው መልእክት ነው። ጳውሎስ ከቁጥር 2-4 የተጠቀሙበት ቋንቋ በከፍተኛ ደረጃ ዘይቤያዊ ነው። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እስራኤላውያን በምድረ በዳ ያሳለፉት ሕይወት ራሳቸው ከክርስቶስ ጋር (በተለይም በቅዱስ ቁርባን ፊት) የሚያሳልፉት ሕይወት መንፈሳዊ መልእክት ሊሆን እንደሚችል እንዲገነዘቡ ፈልጓል።

በዚህ ዘመን ያለን አንባቢዎች ይህንን ምስያ ጳውሎስ በገለጸው መንገድ ለመረዳት መቻላችን አጠራጣሪ ነው። ጳውሎስ ባይነግረን ኖሮ ደመናውንና ባሕሩን ከጥምቀት (ቁ. 2)፥ ወይም ዓለቱን ከክርስቶስ ጋር (ቁ. 4) እናመሳስል ነበር? በሌላ አገላለጽ፥ በራሳችን አነሣሽነት በተወሰነ የእርግጠኝነት መጠን የተሟላ ወይም ሁለተኛ ፍች ለመስጠት እንደፍራለን ወይ? መልሱ አንደፍርም የሚል ይሆናል። መንፈስ ቅዱስ የተለመደውን የዓውደ ንባብ፥ የፍላጎት፥ የስልትና የቃላት አጠቃቀም ሕግጋት (ከዚህ በላይ *ነቢይ ወደፊት የሚሆነውን አመልካች* የሚለውን ተመልከት) ሳይከተል ጳውሎስ እስራኤላውያን በምድረ በዳ የነበሩበት ሁኔታ ከክርስቲያኖች ሕይወት ጋር እንደሚመሳሰል አድርጎ እንዲጽፍ መርቶታል። መንፈስ ቅዱስ እስራኤላውያን ከአንድ ጊዜ በላይ ውኃ ከድንጋይ ፈልቆ መጠጣታቸው ዓለቱ ስለተከተላቸው የመሆኑን እውነት ባልተለመደ ዘይቤያዊ አገላለጽ እንዲናገር ጳውሎስን መርቶታል። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡1-4 የሚጠቀምባቸው ሌሎች ዝርዝሮችም (ቀጥተኛ ያልሆኑ በቁጥር 1 እንደ «አባቶቻችን ሁሉ»፥ በቁጥር 3-4 «መንፈሳዊ» ምግብና መጠጥ) ያሉት በሚያስገርም ሁኔታ ያልተለመዱ ናቸው።

እኛ ግን በመንፈስ ቅዱስ የተመራን የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች አይደለንም። እኛ ጳውሎስ ያደረገውን የማድረግ ሥልጣን የለንም። በብሉይና አዲስ ኪዳን መካከል ያገኛቸው ስውር መንፈሳዊ መልእክቶች ( ልል ግዞር ስ) ተአማኒነት ያላቸው ናቸው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በየትም ስፍራ፥ «እናንተም እንደዚህ አድርጉ» አይለንም። ስለሆነም *የተሟላውን ፍች የመፈለጉ መርህ ሥራ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር እንጂ የአብርሆት ድርሻ አይደለም።* አንድን ምንባብ ለመጻፍ የብሉይ ኪዳኑን ደራሲ ያነሣሣው ያው መንፈስ ቅዱስ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊም የተለመዱ የዓውደ ንባብ፥ የፍላጎት፥ የስልትና የቃላት አጠቃቀም መመዘኛዎችን አልፎ የብሉይ ኪዳኑ ምንባብ ሁለተኛ ፍች እንዳለው እንዲያመለክት ሊመራው

ይችላል። እኛ ግን አብርሆት የተሰጠን አንባቢዎች እንጂ፥ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ያረፈብን ደራሲያን አይደለንም። እስትንፋሰ-እግዚአብሔር (inspiration) ደራሲያኑ መጽሐፍ ቅዱስን በተወሰነ መንገድ እንዲጽፉ የተሰጣቸው የመጀመሪያ ማነሣሻ ነው። አብርሆት (illumination) የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲያን የጻፉትን አሳብ የመረዳት ሂደት ነው። በአብርሆታችን መጽሐፍ ቅዱስን እንደገና ልንጽፍ ወይም አዲስ ፍች ልንሰጥ አንችልም። ስለሆነም በአዲስ ኪዳን እስካልተነገረን ድረስ እኛ በራሳችን ሥልጣን የብሉይ ኪዳን ምንባብን የተሟላ ፍች ልንሰጥ አንችልም።

የጥናት መጽሐፍ ቅዱሶች፥ ማብራሪያዎች፥ የመመሪያ መጻሕፍትና የማጣቀሻ ዓምዶች ያሏቸው መጻሕፍት ሁሉ በአዲስ ኪዳን ሁለተኛ ፍች ያሏቸውን የብሉይ ኪዳን የትንቢት ምንባቦችን ያመለክታሉ። አዲስ ኪዳን ሁለተኛ ፍች ከሚሰጥባቸው ክፍሎች መካከል ማቴ. 1፡22-23 (ኢሳ. 7፡14)፥ 2፡15 (ሆሴዕ 11፡1)፤ 2፡17-18 (ኤር. 31፡15)፥ ዮሐ. 12፡15 (ዘካ. 9፡9) ይገኙባቸዋል።

ሁለተኛ ፍች በትንቢታዊ መልእክቶች ውስጥ የሚታይበትን ሁኔታ ለማብራራት ከእነዚህ መካከል አንዱን ብቻ እንመለከታለን። ማቴዎስ 2፡15። በሆሴዕ 11፡1 የሚከተለውን እናነባለን፡-

*«እስራኤል ገና ሕፃን ሳለ ወደድሁት፤*

*ልጄንም ከግብፅ ጠራሁት።»*

የሆሴዕ ዓውድ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት እንዳወጣቸው የሚገልጽ ነው። ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት ደግሞ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንደ ልጁ እንደሚወዳቸው ለማሳየት ነው። ስልቱ ተመሳሳይ ትይዩነት ሲሆን፥ «ልጄ» የሚለው ከ«እስራኤል» ጋር ተጣምሯል። የቃላት አጠቃቀሙ ዘይቤያዊ ነው። በዚህ ክፍል እስራኤል ሰውኛ የሆነ (ልጅ) የአገላለጽ ዘይቤ እንደተሰጣት ግልጽ ነው። ከዚህ ምንባብ «ግልጽ» መልእክት የሥላሴ ሁለተኛ አካል የሆነው ክርስቶስ አልተጠቀሰም።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ማቴዎስ 2፡15 ባይኖር ኖሮ፥ ይህንን የሆሴዕ ምንባብ ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተነገረ ትንቢት ልንወስደው አንችልም ነበር። ነገር ግን ማቴዎስ እኛ የሌለን አንድ ነገር ነበረው። ሆሴዕ 11፡1ን እንዲጽፍ የመራው ያው መንፈስ ቅዱስ ለእርሱም ይህንኑ ሥልጣን ሰጥቶት ነበር። ይኸው መንፈስ ቅዱስ ሆሴዕ የተጠቀመባቸው ቃላት በሌላ ዓውድ፥ ፍላጎትና ስልት፥ ከሌሎች ቃላት ጋር ስለ መሢሑ ዳግም ሊያገለግሉ እንደሚችሉ እንዲወስን

አነሣሣው። መንፈስ ቅዱስ እነዚያን ቃላት በሆሴዕ መጽሐፍ ውስጥ «የተከላቸው» ከክርስቶስ ሕይወት ጋር በተያያዘ ለማገልገል በሚያመች መልኩ ነበር። ማቴዎስ እነዚያን ቃላት ለክርስቶስ የተጠቀመው ከሐቲታዊ – ሥነ አፈታታዊ መርህ ወይም ሂደት አንጻር አይደለም። ይልቁንም እነዚያን ቃላት ከመጀመሪያው ዓውዳቸው አውጥቶ ፍጹም በተለየ ፍች ተጠቅሞባቸዋል። እኛ እርሱ ያደረገውን አንብቦ ከማድነቅ የተሻለ ሚና የለንም። በራሳችን አነሣሽነት ለየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሁለተኛ ፍች ልንሰጠው አንችልም።

### *የመጨረሻው ጥቅም፡ በዶክትሪናዊና በሕይወት ንጽሕና (Orthodoxy and Orthopraxy) ላይ መንታ ትኩረት*

ዶክትሪናዊ ንጽሕና ትክክለኛ እምነት ሲሆን፥ የሕይወት ንጽሕና ትክክለኛ ተግባር ነው። እግዚአብሔር ጥንታዊ የእስራኤልና የይሁዳ ሕዝቦችን ትክክለኛ እምነትና ትክክለኛ ተግባር ሚዛናዊ ወደሆነበት ሕይወት በነቢያቱ አማካኝነት ሲጠራቸው ኖሯል። ይህ ደግሞ አዲሱ ኪዳንም የሚፈልገው ሚዛናዊነት ነው (ያዕ. 1፥27፤ 2፥18፤ ኤፌ. 2፥8–10)። በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ እግዚአብሔር ከእስራኤልና ከይሁዳ የፈለገው ከእኛም የሚፈልገው ነው። ነቢያቱ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ለማስጠበቅ እንደሚሻ በተከታታይ ሊያስገነዝቡን ይችላሉ። የአዲስ ኪዳንን ሕግጋት (እግዚአብሔርንና ባልንጀራን መውደድ) ለሚጠብቁ ሰዎች (ምንም እንኳ ውጤቶችን በዚህ ዓለም የማግኘቱ ጉዳይ ያንን ያህል ባይበረታታም) የፍጻሜውና ዘላለማዊው ውጤት በረከት ይሆናል። ለማይታዘዙት ግን የምድር ላይ ቆይታቸው ምንም ያህል የተሳካ ቢሆንም፥ ውጤቱ መርገም ብቻ ይሆናል። የሚልክያስ ማስጠንቀቂያ ዛሬም አልተነሣም (ሚልክ. 4፥6)።

# መዝሙረ ዳዊት፡ የእስራኤልና የእኛም ጸሎቶች

የዕብራውያን ጸሎቶችና መዝሙራት ስብስብ የሆነው መዝሙረ ዳዊት ምናልባትም ለአብዛኞቹ ክርስቲያኖች እጅግ የሚታወቅና የሚወደድ የብሉይ ኪዳን ክፍል ነው። ብዙውን ጊዜ መዝሙረ ዳዊት ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር አብሮ መታተሙና ለአምልኮ መዋሉ፥ ለመጽሐፉ ተወዳጅነት የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህም ሆኖ፥ መዝሙረ ዳዊት ብዙውን ጊዜ ሰዎች አሳቡን ሳይረዱ በመሰላቸው መንገድ የሚጠቀሙበት መጽሐፍ ነው።

የመዝሙረ ዳዊት አተረጓጎም ችግር የሚነሣው በቀዳሚነት ከባሕርዩ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ፥ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በውስጥ ያለው አሳብ ሁሉ ከእግዚአብሔር ወደ ሰዎች የተላከ እንደሆነ ያስባሉ። በዚህም ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለእግዚአብሔር ወይም ስለ እግዚአብሔር የተነገሩ ቃላት እንዳሉና እነዚህም ደግሞ የእግዚአብሔር ቃላት እንደሆኑ ከመረዳት ይታቀባሉ።

በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የሚገኙ መዝሙራትም እንዲህ ዓይነት ቃላት ናቸው። መዝሙራት በባሕርያቸው ጸሎቶችና የአምልኮ ዝማሬዎች በመሆናቸው ወደ እግዚአብሔር እንዲደርሱ የታሰቡ ወይም ስለ እግዚአብሔር በመዝሙር እውነትን የሚገልጹ ናቸው። ይህም የተለየ የአሁንዚያ ችግር ይፈጥርብናል። እነዚህ ለእግዚአብሔር የተነገሩ ቃላት ለእኛ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚያገለግሉት እንዴት ነው? መዝሙራት ምክሮችንና፥ ትእዛዛትን፥ ወይም ዶክትሪኖችን የሚያብራሩ ታሪኮች ባለመሆናቸው፥ በቀዳማይነት ዶክትሪን ወይም የሥነ ምግባር ባሕርይ ለማስተማር አያገለግሉም። ነገር ግን እግዚአብሔር በአስትንፋሱ ላቀዳቸው ዓላማዎች ስንጠቀምባቸው ፍሬያማ ይሆናሉ። እነዚህም ዓላማዎች፥ (1) ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንድንገልጽና (2) መንገዶቹን እንድናስብ መርዳት ናቸው። ስለሆነም መዝሙራት ኀዘንና ደስታን፥ ስኬትንና ውድቀትን፥ ተስፋንና ጸጸትን ለመግለጽ የመጽሐፍ ቅዱስን ድጋፍ ለሚሻ አማኝ እጅግ ጠቃሚዎች ናቸው።

ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች መዝሙራትን በትክክል ስለማይረዱቸው በተሳሳተ መንገድ ከሕይወታቸው ጋር ሲያዛምዱቸው እናያለን። ሁሉም (ለምሳሌ እንደ መዝሙር 23) በአመክኒዮአዊ (Reason) መንገድ ለመከተል ወይም ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ጋር ለማዛመድ የሚቀሉ አይደሉም። በመዝሙር 23 ተምሳሌታዊ

አቀራረብ እግዚአብሔር እንደ እረኛ፥ ዘማሪው (እና እኛም) እንደ በጎቹ ሁነው ተገልጸዋል። በዚህ መዝሙር ውስጥ እግዚአብሔር በተስማሚ መስኮች ውስጥ በማሰማራት፥ ማለትም የሚያስፈልገንን ሁሉ በማሟላት፥ በመጠበቅና በመንከባከብ ቸርነቱን እንደሚያደርግልን ተመልክቷል።

ሌሎች መዝሙሮች ግን ፍችያቸውን በፍጥነት አይገልጹልንም። ለምሳሌ፥ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ በአሉታዊ መንገድ የተገለጸውንና የተናጋሪውን ሥቃይ የሚያትተውን መዝሙር እንዴት መጠቀም ይቻላል? ይህ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ልንጠቀምበት የሚገባን ነው ወይስ ለግል ግልጋሎት ብቻ? ስለ እስራኤል ታሪክና እግዚአብሔር እነርሱን ስለባረከበት ሁኔታ የሚናገሩ መዝሙሮችስ? ዛሬ ያለው ክርስቲያን እንዲህ ዓይነቶቹን መዝሙሮች በሚገባ መጠቀም ይችላል ወይስ ይህ ከአይሁዶች ውጭ ላሉት አይቻልም? ስለ መሢሑ ሥራ የሚተነብዩ መዝሙራትስ? የጥበብን ጥቅም የሚያጎሉ መዝሙራትስ? የእስራኤልን ነገሥታት ክብር የሚያወድሱ መዝሙራትስ? በአሁኑ ጊዜ በነገሥታት የሚገዙ የዓለም አገሮች በጣም ጥቂቶች በመሆናቸው ይህንኑ የንግሥና ጉዳይ መረዳቱ ቀላል ሊሆን አይችልም። በመጨረሻም፥ የባቢሎናውያን ልጆች በዓለት ላይ እንዲፈጠፈጡ የሚቀርበውን ምኞት እንዴት መመልከት ይቻላል? [መዝ. (137)፡8–9]።

የመዝሙራትን ዓይነቶችና ሊያገለግሉ የሚችሉባቸውን መንገዶች በሙሉ ለመዳሰስ ትልቅ መጽሐፍ የሚጠይቅ መሆኑ እሙን ነው። ስለሆነም በዚህ ምዕራፍ መዝሙራትን በግል ሕይወትህና በምታመልክበት ቤተ ክርስቲያን በተሻለ መንገድ እንድትገነዘብ የሚያግዙህን አንዳንድ መመሪያዎች እንሰጥሃለን።

## አንዳንድ የመነሻ ሐቲታዊ ምልከታዎች

እንደ ሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ሁሉ፥ መዝሙራት ልዩ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ስላላቸው ለማንበብም ሆነ ለመተርጎም ልዩ ጥንቃቄ ማድረግን ይጠይቃሉ። ይህም ማለት ዓይነቶቻቸውን፥ ቅርጾቻቸውንና አገልግሎታቸውን ጨምሮ ባሕርያቸውን መገንዘብን ይጠይቃል።

### *መዝሙራት እንደ ግጥም*

ምናልባትም መዝሙራትን በምናነብበትም ሆነ በምንተረጉምበት ጊዜ ልናስታውስ የሚገባን እጅግ አስፈላጊው ነገር ሙዚቃዊ ግጥሞች የመሆናቸው ጉዳይ ነው። ምንም እንኳ ስለ ዕብራውያን ግጥሞች

ቀደም ብለን በአጭሩ የተመለከትን ብንሆንም፥ ከመዝሙራት ጋር በተያያዘ ሦስት ተጨማሪ ነጥቦችን መገንዘብ ይኖርብናል።

1. የዕብራይስጥ ግጥም በባሕርዩ በልብ በኩል ወደ አእምሮ እንደሚላክ መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። (ይህም ማለት አብዛኛው የቋንቋ አገላለጽ ሆን ተብሎ በስሜት ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል።) ስለሆነም፥ ከእያንዳንዱ ቃል ወይም ሐረግ ደራሲው ሊያስተላልፍ ያልፈለገውን ልዩ ትርጉም ለማግኘት መሞከር የለብንም። ለምሳሌ፥ በዕብራውያን ግጥም ውስጥ ሁልጊዜም አንድ ዓይነት ትይዩነት እንደሚኖርና «ተመሳሳይ ትይዩነት» (ሁለተኛው ስንኝ የመጀመሪያውን ስንኝ ስሜት መልሶ የሚያስተጋባበት የግጥም ዓይነት) የሚባል የተለመደ አገባብ እንዳለ ታስታውሳለህ። በእንደዚህ ዓይነት ግጥሞች ውስጥ ሁለቱም መስመሮች በጋራ የሚገልጹት ገጣሚው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት ነው። ሁለተኛው መስመር አዲስ ወይም የተለየ አሳብ ለማስተላለፍ አይሞክርም። ለምሳሌ ያህል፥ መዝሙር 19፡1ን አንብብ።

ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥

የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።

ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፥

ሌሊትም ለሌሊት እውቀትን ትናገራለች።

በእነዚህ ሁለት ተመሳሳይ ትይዩ ግጥሞች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተነሣሣው ገጣሚ እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ አምላክ ሲያመሰግነው እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱስ ተመሳሳይ ትይዩ አሳቦችን ለመለየት ነጠላ ሰረዝ /፥/ በመጠቀም ትይዩ አሳባቦችን እንድትገነዘብ እንደረዳህ አስተውል።

የገጣሚው ነጥብ በዝርው አጻጻፍ ቢገለጽ፥ «እግዚአብሔር በፍጥረቱ በተለይም ደግሞ በሰማያዊ አካላት ተገልጾአል» የሚል ይሆናል። ነገር ግን ከመዝሙሩ ውብ ግጥም ጋር ሲነጻጸር ይኼኛው ዝርው አጻጻፍ ጣዕም–አልባ ሆኖ እናገኘዋለን። የግጥሙ የላቀ የቋንቋ አጠቃቀም በተሻለ ሁኔታ አሳቡን ከመግለጹ በላይ ይበልጥ ሊታወስ በሚችልበት መልኩ ያስቀምጠዋል። ምንም እንኳ ሁለተኛው ክፍል በቀንና በሌሊት ሰማያት ፈጣሪያቸውን እንደሚገልጹ የሚያስረዳ አሳብ ቢጨምርም፥ አራቱ መስመሮች አራት የተለያዩ አሳቦችን የሚያስተላልፉ አይደሉም። ነገር ግን በመጀመሪያው ክፍል ዘማሪው ሰማያት አንድ ነገር፣ የሰማይ ጠፈሮች ደግሞ ሌላ ነገር ያደርጋሉ

አይልም። ሁለቱ መስመሮች በአንድነት ስለ አንድ የከበረ እውነታ ይናገራሉ።

2. መዝሙራት የትኛውም ዓይነት ግጥሞች ሳይሆኑ ሙዚቃዊ ግጥሞች መሆናቸውን መገንዘብ ያሻል። ሙዚቃው ግጥምን እንደ መልእክት፥ ትረካ ወይም የሕግ ክፍል አድርጎ ማንበብ አይቻልም። ሙዚቃው ግጥም እንድናስብ ለማገዝ ሳይሆን ለስሜታችን እንዲቀርብ ሆኖ የተጻፈ ነው። ይህም በመሆኑ የተወሰኑ አሳቦችን ከማወቅ ያለፈ ምላሽን የማቀጣጠል ብቃት ይኖረዋል። ምንም እንኳ መዝሙራት ዶክትሪን—አዘል ቢሆኑም፥ የዶክትሪን ጎተራዎች ግን አይደሉም። አንድን ትረካ የዶክትሪን ሥርዓት አድርጎ መውሰዱ አደገኛ እንደሆነ ሁሉ፥ አንድን መዝሙር እንደ ዶክትሪን መማሪያ መመልከቱም አደገኛ ነው። መዝሙራት አንዳንድ ጉዳዮችን በሙዚቃዊና ግጥማዊ ቃና መዳሰሳቸው አንድን ነገር የገለጹበት መንገድ ለአመክኒዮአዊ (Reason) ክርክር ሊያነሣሣን አይገባም።

ስለ «መሸሸጊያ ዋሻ»ን ስንዘምር ስንቶቻችን ነን እግዚአብሔርን በቀጥታ ከዋሻ ጋር የምናዛምድ? ይህ ስለ እግዚአብሔር የምናስብበት ተምሳሌታዊ አገላለጽ እንደሆነ እንገነዘባለን። በተመሳሳይ ሁኔታ መዝሙረኛው «እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ» ሲል [መዝ. (51):5]፥ መፀነስ ኃጢአት እንደሆነ፥ የፀነሰችው ሴት በመፀነሷ ኃጢአትን እንደፈጸመችና ባልተወለዱ ልጆች ላይ የአዳም ኃጢአት እንደሚጋባ ወይም እንዲህ ዓይነት ዶክትሪን መመሥረቱ አልነበረም። ነገር ግን መዝሙረኛው ኃጢአተኛነቱን ጠንከር አድርጎ በግልጽ ለማስቀመጥ ሲል ግነት ተጠቅሟል። አንድን መዝሙር በምታነብበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የጻፈው ገጣሚ ያልፈለገውን አሳብ ለማውጣት መሞከር የለብህም።

3. ግጥም ሆነ ተብሎ በዘይቤያዊ ቃላት እንደሚጻፍ ማስታወሱም በእኩል ደረጃ ጠቃሚ ነው። ስለሆነም የዘይቤውን ዓላማ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባቱ አስፈላጊ ነው። በመዝሙራት ውስጥ ኮረብቶች እንደ በግ ጠቦቶች ሲዘሉ [(114):6]፤ ከግብጽ በወጡበት ጊዜ ስላጀቧቸው ተአምራት መዘመሩ እንዴት ታላቅ ነገር ነው!)፥ ጠላቶች ከአፋቸው ሰይፍን ሲተፉ [(59):7]፤ በውሸት ስለት ተወግቶ ያልቆሰለ ማን አለ?) እና እግዚአብሔር እንደ እረኛ፥ ግንብ፥ ጋሻና ዓለት ሲሣል እንመለከታለን። እነዚህን ዘይቤዎች «ሰምተህ» ምንን እንደሚወክሉ ማወቅህ በጣም አስፈላጊ ነው።

እንዲሁም ደግሞ ዘይቤዎችን ሳናስላስል ቀጥታ አለመውሰዱ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፥ አንድ ሰው መዝሙር 23ን በቀጥታ አንብቦ

እግዚአብሔር እንደ በጎች እንድንሆን እንደሚፈልግ ወይም የገጠርን የከብት አርቢነት ሕይወት እንድንመራ እንደሚሻ በማሰብ ሊሳሳት ይችላል። ይህም ክፍሉ የከተማን ሕይወት ይቃወማል ብለን እንድንጠቅስ ያደርገናል። ተምሳሌታዊ ቋንቋን (ተለዋጭና ተነጻጻሪ ዘይቤን) አለመረዳትና የመዝሙሩን ረቂቅ አሳቦች ወደ ተጨባጭ ሁኔታ ለመመለስ አለመቻል፥ ወደ ተሳሳተ ተዛምዶ ሊመራን ይችላል።

## *መዝሙራት እንደ ሥነ ጽሑፍ*

ሙዚቃዊ ግጥሞች የሆኑት መዝሙራት የሥነ ጽሑፍ ዓይነትም በመሆናቸውና ስታነባቸው ወይም ስታጠናቸው የተወሰኑ ሥነ ጽሑፋዊ ገጽታዎቻቸውን መለየት ይኖርብሃል። እነዚህን አለመረዳቱ አንድ ሰው አያሌ የተሳሳቱ አተረጓጎሞችንና ተዛምዶዎችን እንዲያካሂድ ሊያደርግ ይችላል።

1. መዝሙራት የተለያዩ <u>ዓይነቶች</u> ናቸው። ይህ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ወደ በኋላ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ስለ መሠረታዊ የመዝሙራት ዓይነቶች በምንነጋገርበት ክፍል ውስጥ እናብራራዋለን። ለአሁኑ ግን እስራኤላውያን እነዚህን ሁሉ የመዝሙር ዓይነቶች ያውቁ እንደነበር መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። በሰቆቃ (መዝሙር አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ኀዘኑን በእግዚአብሔር ፊት አፍስሶ እርዳታ የሚጠይቅበት) እና በምስጋና መዝሙር (ደግሞ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን እግዚአብሔር ላሳየው ምሕረት ምስጋናውን የሚገልጽበት) መካከል ያለውን ልዩነት ያውቁ ነበር። በባሕላችን እንደ እስራኤላውያን መዝሙራትን አዘውትረን አንጠቀምም። ስለሆነም፥ አንድ ሰው የሚያነበውን የመዝሙር ዓይነት የማያውቅ ከሆነ ለመረዳት እንደሚቸገር የታወቀ ነው።

2. እያንዳንዱ መዝሙር <u>በቅርጹ</u> ይለያል። ቅርጽ ስንል ከተመሳሳይ የመዝሙር ዓይነቶች ጋር የሚጋሯቸውን ባሕርያት (በተለይም መዋቅር) በመገንዘብ የተወሰነ የራሱ ዓይነት ማለታችን ነው። አንድ ሰው የአንድን መዝሙር መዋቅር በሚረዳበት ጊዜ በመዝሙሩ ውስጥ የሚሆነውን ለመከተል አይቸገርም። ለምሳሌ፥ መዝሙረኛው ከአንድ ርእሰ ጉዳይ ወደ ሌላው የሚያደርገውን ሽግግር፥ ለጉዳዮቹ የሚሰጠውን የትኩረት መጠን በመገንዘብ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት መጨበጥ ይቻላል። ይህንን ወደ በኋላ ከምናቀርበው ያኔዚያዊ ናሙና ልትመለከት ትችላለህ።

3. እያንዳንዱ የመዝሙራት ዓይነት በእስራኤል ሕይወት ውስጥ የተወሰነ <u>ድርሻ</u> እንዲኖረው የታሰበ ነው። ይህም ጉዳይ ጠቃሚ በመሆኑ ወረድ ብለን እንመለከተዋለን። ለአሁኑ እያንዳንዱ መዝሙር

የታቀደለት ዓላማ እንዳለው መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፥ ለእስራኤል ንጉሣውያን ሊውል የሚገባውን የንግሥና መዝሙር ለሰርግ መጠቀሙ ትክክል አይሆንም። መዝሙሩ ከሰርግ ሥነ ሥርዓት ጋር እንዲስማማ ተደርጎ አልተዘጋጀምና።

4. እንዲሁም ደግሞ በመዝሙራት ውስጥ የተለያዩ ገጽታዎችን መለየቱ አስፈላጊ ነው። የመዝሙራት ደራሲያን ቃላትንና ድምፆችን በተወሰኑ መንገዶች በመደርደርና በመደጋገም፥ እንዲሁም ደግሞ በቃላት ደስ የሚሰኙ ይመስላል። በተጨማሪም፥ የአንዳንድ መዝሙሮች የመጀመሪያ መስመር ወይም ጥቅስ ፊደላት የፊደል ገበታን ( ሀ ለ ሐ መ ) ቅደም ተከተል ጠብቀው የሚጓዙ ይሆናሉ። መዝሙር 119 ለዚህ በአብነት ሊጠቀስ ይችላል። የቁጥር አሰጣጡና ድግግሞሹ አንባቢው አማኙ የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ ስለሚያገኛቸው በረከቶችና መወጣት ስለሚገባቸው ኃላፊነቶች እንዲገነዘብ ይመራዋል።

5. በመጨረሻም፥ እያንዳንዱ መዝሙር እንደ <u>ሥነ ጽሑፋዊ አሐድ</u> (literary unit) መነበብ ይኖርበታል። መዝሙራትን በወጥነት መረዳት እንጂ እያንዳንዱን ቁጥር ለብቻው መነጠሉ ተገቢ አይሆንም። ማለትም ደግሞ እንደ መጽሐፈ ምሳሌ እያንዳንዱን ቁጥር ከጠቅላላው ለይቶ ማሰቡ ትክክለኛውን መልእክት ለመጨበጥ አይረዳም። በንባብ ወቅት የመዝሙሩን ፍሰትና ሚዛን መከተሉ ጠቃሚ ነው። እያንዳንዱ መዝሙር አሳቡ የሚቀርብበት፥ የሚጎለብትበትና ወደ አንድ ዓይነት ማጠቃለያ የሚመጣበት አሠራር አለው።

ስለሆነም፥ የትኛውም መዝሙር ከሌሎች ጋር ሥነ ጽሑፋዊ ጥምረት ስላለው፥ ከመዝሙሩ ውስጥ ቁጥሮችን ለብቻቸው እያወጡ ያለዓውዳቸው መተርጎሙ ትክክል አይሆንም። ለምሳሌ፥ መዝሙር (105)፡34ን ተመልከት! «ተናገረ፥ አንበጣም ስፍር ቁጥር የሌለውም ኩብኩባ መጣ፥» ከዓውደ ንባቡ ውጭ ብንመለከት፥ ይህ ቁጥር እግዚአብሔር አንበጣዎችንና ኩብኩባዎችን በምድር ላይ ለሆነ ዓላማ እንደጠራቸው ወይም ቃሉ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በአንበጣዎችና በኩብኩባዎች አማካኝነት እንደተፈጸመ ሊያመለክት ይችላል። ይህንን፥ «እግዚአብሔርም በጎ ነገር ይሰጣል፥ ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች» ከሚለው ከመዝሙር (85)፡12 ጋር እንዴት ማነጻጸር ይቻላል? ምክንያቱም አንበጣዎችና ኩብኩባዎች ምድርን የሚያጠፉ መሆናቸው በኢዩኤል 2፡25 ተገልጾአል። የእግዚአብሔር ቃል አንበጣዎችን እንደሚያመጣ እየተናገረ ምድር ፍሬዋን እንዳትሰጥ እንደሚያደርግ እንዴት ቃል ሊገባ ይችላል? እነዚህ ሁሉ ቁጥሮች በሚካተቱበት ሙዚቃዊ ግጥም ሙሉ ዓውደ ንባብ ውስጥ፥ ከቁጥሮቹ ለቃላቱ ብያኔ

እንድንለጥና ዓውደ ንባቡን ባለማወቃችን ምክንያት ራሳችን በምንፈጥረው ፍላጎት ሳይሆን በራሱ በገጣሚው ፍላጎት መሠረት እንድንረዳው የሚያግዝ የፍች መዋቅር እንዳለ በመገንዘብ ለጥያቄው ምላሽ መስጠት ይቻላል። መዝሙር (85) እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል ታማኝ መሆኑን በማሳየት፥ የእስራኤልን ምድር እንደሚባርክ ያስረዳል። መዝሙር (105) እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነፃ ለማውጣት በፈርዖን ላይ በመቅሰፍትነት ስላመጣቸው አንበጣዎችና ኩብኩባዎች ይናገራል። ስለሆነም የእነዚህን መዝሙሮች ክፍሎች ከዓውደ ንባባቸው ውጭ መጠቀሙ ወደ ተሳሳቱ ተዛምዶዎች እንደሚመራ ልንመለከት እንችላለን። አንድ ሰው የአንድ ጽሑፍን ቁራጭ ወስዶ በተሳሳተ መንገድ በሚጠቀምበት ጊዜ፥ ያ ጽሑፍ እንዲጫወት የተፈለገውን ሚና የመጫወት ብቃት ያንሰዋል። የአንድን መዝሙር የተወሰነ ክፍል እንኳ በተሳሳተ መንገድ ብናዛምድ፥ እግዚአብሔር ክፍሉን የሰጠባቸው ዓላማዎች ከፍጻሜ ሳይደርሱ ይቀራሉ ማለት ነው።

## በጥንቷ እስራኤል የመዝሙራት አጠቃቀም

በጥንቷ እስራኤል መዝሙራት ለአምልኮ እንዲያገለግሉ ተደርገው የተዘጋጁ ተግባራዊ ዝማሬዎች ናቸው። ተግባራዊ ስንል እንደ አሁኑ ዘመን ሕዝቡን ለስብከት ለማዘጋጀት የሚቀርቡ መዝሙሮች ብቻ አልነበሩም ማለታችን ነው። ይልቁንም በአምላኪውና በአምላኩ መካከል ግንኙነትን በመፍጠር መዝሙራት ከፍተኛ አገልግሎት ያበረክቱ ነበር።

አብዛኞቹ መዝሙሮች መቼ እንደተጻፉ በትክክል ማረጋገጥ አይቻልም። ይህ ግን ትልቅ ያኔዚያዊ ችግር አይደለም። መዝሙራት በሚያስደንቅ ሁኔታ ለዘመናት ሁሉ የሚያገለግሉ ናቸው። በጥንታዊቷ እስራኤል የነበራቸው ጥቅም ለእኛ ትምህርት የሚሰጥ ቢሆንም፥ እምብዛም ባለፈው ዘመን አምልኮና ጸሎት ውስጥ ወስኖ አያስቀምጠንም። ለአንድ አማኝ ወይም በቡድን ለሚያመልኩ አማኞች ልብ የሚናገሩ እንደ መሆናቸው፥ የመዝሙራት ባሕላዊና መልክዓ ምድራዊ እሴት በግልጽ ይታያል።

በጥንት ዘመን እስራኤላውያን መሥዋዕቶቻቸውን ይዘው ወደ ኢየሩሳሌሙ ቤተ መቅደስ በሚመጡበት ጊዜ መዝሙራት የአምልኮ አጋዦች ሆነው ያገለግሏቸው ነበር። ምንም እንኳ ማረጋገጫ ባይኖረንም፥ ሕዝቡ በሚያመልኩበት ጊዜ የሙዚቃ ባለሙያዎች አንዳንድ ጊዜ በዝማሬ ሳያገለግሉ አይቀሩም። ነገር ግን ከቤተ መቅደሱ ውጭ ሰዎች መዝሙሮችን እያወቁ በመሄዳቸው ሰዎች የራሳቸውን

ሁኔታዎችና አመለካከቶች በሚገልጹ መንገዶች መጠቀማቸው አልቀረም። በመጨረሻም፥ መዝሙራቱ ተሰብስበው «መጽሐፍ» ሆኑ። በዚህ ሁኔታ የተዘጋጁ አምስት መዝሙሮች ነበሩ። (መጽሐፍ 1፡ ከ1–41፤ መጽሐፍ 2፡ 42–72፤ መጽሐፍ 3፡ 73–89፤ መጽሐፍ 4፡ 90–106፤ መጽሐፍ 5፡ 107–150)። የተወሰኑ የመዝሙራት ቡድኖች ልዩ ባሕርያት ስላሏቸው፥ መጀመሪያ በንዑስ ምድቦች የተሰበሰቡ ይመስላል። እነዚህም ኋላ በአምስት ዐበይት መጻሕፍት ውስጥ ተካትተዋል። ነገር ግን እነዚህ ምድቦች አሁን መዝሙረ ዳዊት በተቀናጀበት ሁኔታ ውስጥ አይታዩም። የዚህም ምክንያት አሁን ባለው አዘገጃጀት ውስጥ የተለያዩ መዝሙሮች ተሰባጥረው መገኘታቸው ነው።

በመጀመሪያዎቹ መዝሙሮች ውስጥ ከሌሉትና ከዚህም የተነሣ እስትንፋሰ እግዚአብሔር እንዳረፈባቸው ከማይቆጠሩ የመዝሙር ርእሶች ለመረዳት እንደሚቻለው፥ ዳዊት ግማሽ ያህሉን ጽፎአል። የእነዚህ መዝሙሮች ጠቅላላ ቁጥር 73 ነው። ሙሴ አንድ (መዝሙር 90)፥ ሰሎሞን ሁለት (መዝሙር 72 እና 127ን)፥ የአሳፍ ልጆች በርከት ያሉ፥ የቆሬም ልጆች እንዲሁ በርከት ያሉ፥ ወዘተ... ጽፈዋል።

እስራኤላውያን ከምርኮ ከተመለሱና ቤተ መቅደሱን እንደገና ከገነቡ በኋላ፥ መዝሙረ ዳዊት በመደበኛ ሁኔታ ሊሰበሰብ ችሏል። በዚህ «የቤተ መቅደስ መዝሙር» ስብስብ ውስጥ መዝሙር አንድ እንደ መግቢያ መጀመሪያው ላይ ሲቀመጥ፥ መዝሙር 150 እንደ ማጠቃለያ መጨረሻ ላይ እንዲገባ ተደርጓል። በአጠቃላይ አይሁዶችና በተለይ ደግሞ ክርስቶስና ደቀ መዛሙርቱ መዝሙራትን በሚገባ ያውቁ እንደነበር ከአዲስ ኪዳን እንረዳለን። ጳውሎስ የመጀመሪያው ምእተ ዓመት ክርስቲያኖች በመዝሙርና በውዳሴ፥ በመንፈሳዊ ዝማሬም እርስ በርሳቸው እንዲጽናኑ አበረታቷቸዋል (ኤፌ. 5፡19፤ ቆላ. 3፡16)። ምንም እንኳ ጳውሎስ ይህንን ምክር ሲሰጥ ስለ አንዳንድ ቀደምት ክርስቲያናዊ መዝሙሮች እያሰበ ሊሆን ቢችልም፥ እነዚህ ሦስቱም ቃላት መዝሙራትን ሊያመለክቱ ይችላሉ።

## የመዝሙራት ዓይነቶች

መዝሙራትን በሰባት የተለያዩ ምድቦች መከፋፈል ይቻላል። ምንም እንኳ እነዚህ ምድቦች በመጠኑ ሊመሳሰሉ ወይም ንዑስ ምድቦችን ሊያበጁ ቢችሉም፥ መዝሙራትን ለመከፋፈልና አንባቢው በተሳለ ሁኔታ እንዲያነብ ሊመሩት ይችላሉ።

እነዚህ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ከሚገኙ መዝሙሮች አብዛኛውን እጅ ይሸፍናሉ። የግልና የጋራ የሰቆቃ መዝሙሮች በአጠቃላይ ከስድሳ በላይ ይሆናሉ። የግል የሰቆቃ መዝሙሮች (ለምሳሌ፥ መዝሙር 3፥ 22፥ 31፥ 39፥ 42፥ 57፥ 71፥ 120፥ 139፥ 142) አንድ ግለሰብ ትግሎቹን፥ መከራውን ወይም ቅይማቱን ለጌታ እንዲገልጽ ያስችሉታል። የቡድን የሰቆቃ መዝሙሮች (ለምሳሌ፥ መዝሙር 12፥ 44፥ 80፥ 94፥ 137) ለግለሰብ ሳይሆን ለአንድ ቡድን ተመሳሳይ ግልጋሎት ይሰጣሉ። ተስፋ ቆርጠሃል? ቤተ ክርስቲያንህ መቀመቅ እየወረደች ያለች መስሎ ይሰማሃል? ነገሮች ለምን በአግባቡ እንደማይሳኩ እያሰበ የሚጨነቅ ቡድን (ትንሽም ሆነ ትልቅ) አባል ነህ? እንዲህ ከሆነ፥ አንተ ለእግዚአብሔር ከምታቀርበው ልመና ጋር ተዛማጅነት ይኖረዋል። የጥንት እስራኤላውያን ሕይወት አመቺ አልነበረም። በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የሚገኙ ሰቆቃዎች የሕዝቡን ጭንቀት በጥልቀትና በግልጽ የሚያሳዩ ናቸው።

## የምስጋና መዝሙሮች

ከስማቸው እንደምንገነዘበው፥ እነዚህ መዝሙሮች የሚያገለግሉት ከሰቆቃ መዝሙሮች ለሚቃረኑ ሁኔታዎች ነው። አንድ ነገር በመሳካቱ፥ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ለታማኝነቱ፥ ለጥበቃውና ለሰጣቸው በረከት ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ ምክንያት በማግኘቱ የሚዘምሯቸው ናቸው። የምስጋና መዝሙሮች አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ለእግዚአብሔር የአመስጋኝነት አሳቦችንና ስሜቶችን እንዲገልጹ የሚያስችሉ ናቸው። በመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ውስጥ ስድስት የቡድን (65፥ 67፥ 75፥ 107፥ 124፥ 136)፥ አሥር የግል (18፥ 30፥ 32፥ 34፥ 40፥ 66፥ 92፥ 116፥ 118፥ 138) የምስጋና መዝሙሮች አሉ።

## የውዳሴ መዝሙሮች

እነዚህ መዝሙሮች የቀደሙትን ችግሮችም ሆነ የአሁኖቹን አስደሳች ሁኔታዎች በቀጥታ ሳይጠቅሱ እግዚአብሔርን ለማንነቱ፥ ለታላቅነቱ፥ ለዓለም ሁሉና ለሕዝቡ ስለሚያደርጋቸው መልካም ትሩፋቶች የሚያመሰግኑ ናቸው። ከመዝሙር 8፥ 19፥ 104፥ እና 148 እንደምንመለከተው፥ እግዚአብሔር የአጽናፈ ዓለሙ ፈጣሪ በመሆኑ ይመሰገናል። ከመዝሙር 66፥ 100፥ 111፥ 114 እና 149 እንደምንመለከተው፥ ለእስራኤል ስለሚያደርገው ጥበቃና በረከትም ይመሰገናል። እንደዚሁም መዝሙር 33፥ 103፥ 113፥ 117፥ 145–147 እንደሚያስረዱት፥ እንደ ታሪክ ጌታም ሲመሰገን እንመለከታለን።

እውነትም እግዚአብሔር ሊወደስና ሊመሰገን ይገባዋል። ስለሆነም እነዚህ መዝሙሮች አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን በአምልኮ ጊዜ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንባቸው ናቸው።

## *የደኅንነት ታሪክ መዝሙሮች*

የሚከተሉት እነዚህ ጥቂት መዝሙሮች (78፥ 105፥ 106፥ 135፥ 136) እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ መካከል የማዳን ሥራውን የገለጸበትን ታሪክ መለስ ብለው ያሳስባሉ። በተለይም ከግብጽ ባርነት አውጥቶ እንደ ሕዝብ እንዴት እንደመሠረታቸው በማሰብ ያመሰግኑታል። የኋላ ኋላ ክርስቶስ የመጣበትና በእርሱም በኩል የእግዚአብሔር ቃል የተሰጠበት የእስራኤል ሕዝብ በሰው ልጅ ታሪክ ታላቅ ሕዝብ ነው። የዚህ ሕዝብ ታሪክ በእነዚህ የደኅንነት የታሪክ መዝሙሮች አማካይነት ተዘክሯል።

## *የበዓላት መዝሙሮች*

በዚህ ክፍል ውስጥ አያሌ የመዝሙር ዓይነቶች ተካትተዋል። የመጀመሪያው መዝሙር 50 እና 81 የሚገኙበት የቃል ኪዳን ማደሻዎች ያሉት ናቸው። እነዚህ መዝሙሮች ሕዝቡ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ የሰጣቸውን ቃል ኪዳኖች እንዲያድሱ የሚያበረታቱ ናቸው። እነዚህም መዝሙሮች ለተሐድሶ አገልግሎት የአምልኮ መመሪያዎች ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። እግዚአብሔር የዳዊትን የዘር ሐረግ የመምረጡን አስፈላጊነት በመግለጽ ምስጋና የሚያቀርቡ እንደ መዝሙር 89 እና 132 ያሉት ብዙውን ጊዜ የዳዊት የቃል ኪዳን መዝሙሮች ክፍል ተደርገው ይወሰዳሉ። ይህ የዘር ሐረግ ወደ ክርስቶስ ልደት ስለሚመራ፥ እነዚህ መዝሙሮች ለመሢሐዊ አገልግሎት መሠረት ይጥላሉ። በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ከንግሥና ጋር የሚዛመዱ ዘጠኝ መዝሙሮች አሉ እነርሱም መዝሙር (2፥ 18፥ 20፥ 21፥ 45፥ 72፥ 101፥ 110፥ 144) ናቸው። ከእነዚህም አንዱ መዝሙር (18) ንጉሣዊ የምስጋና መዝሙር ሲሆን፥ ሌላው መዝሙር (144) ንጉሣዊ የሰቆቃ መዝሙር ነው። እግዚአብሔር መረጋጋትንና ጥበቃን የሚሰጥበት መንገድ በመሆኑ፥ በጥንታዊት እስራኤል ንግሥና ጠቃሚ ተቋም ነበር። ምንም እንኳ ብዙዎቹ ነገሥታት ለእግዚአብሔር ታማኞች ባይሆኑም፥ የትኞቹንም ለመልካም ዓላማዎች ሊጠቀምባቸው ይችል ነበር። እግዚአብሔር በማኅበረሰቡ ውስጥ የአስታራቂነትን (አማላጅነት) ተግባር በሚያከናውኑ ሰዎች አማካኝነት ስለሚሠራ፥ ለእነዚህ መካከለኞች አገልግሎት የቀረበውን ምስጋና የምንመለከተው በንግሥና መዝሙሮች ውስጥ ነው።

ከንግሥና መዝሙሮች ጋር የሚዛመዱ የዙፋን መዝሙሮችም አሉ (24፥ 29፥ 47፥ 93፥ 95–99)። እነዚህ መዝሙሮች በጥንታዊቷ እስራኤል የአንድን ንጉሥ ወደ ዙፋን መውጣት የሚያከብሩ ሳይሆኑ አይቀሩም። ይህም ምናልባት በየዓመቱ የሚካሄድ በዓል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ምሁራን እነዚህ መዝሙሮች የጌታን በዙፋን ላይ መሆን እንደሚያመለክቱም ገልጸዋል። ለዚህ አሳብ መረጃ ማቅረቡ አስቸጋሪ ቢሆንም፥ አመለካከቱ ትክክል ከሆነ ከዚህ ጋር የሚካሄዱ ሥርዓቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

በመጨረሻም የጽዮን መዝሙሮች ወይም የኢየሩሳሌም ከተማ መዝሙሮች (46፥ 48፥ 76፥ 84፥ 87፥ 122) የሚባሉ ናቸው። እስራኤላውያን ገና ምድረ በዳ ውስጥ ሳሉ በሙሴ በኩል እንደተነበየላቸው (ለምሳሌ፥ በዘዳግም 12)፥ ኢየሩሳሌም የእስራኤል መዲና፥ የቤተ መቅደሱ ማረፊያና የንጉሥ ዳዊት የሥልጣን ምንጭ ለመሆን በቅታለች። በእነዚህ መዝሙሮች ኢየሩሳሌም እንደ «ቅድስት ከተማ» ልዩ ትኩረትና አክብሮት ተሰጥቷታል። አዲስ ኪዳን አዲስቱን ኢየሩሳሌም የመንግሥተ ሰማይ ተምሳሌት ስለሚያደርጋት እነዚህ መዝሙሮች በክርስቲያን አምልኮ ውስጥ ጠቃሚዎች ሆነው ይኖራሉ።

### *የጥበብ መዝሙሮች*

በዚህ ምድብ ውስጥ ስምንት መዝሙሮች ሊካተቱ ይችላሉ። እነርሱም፤ 36፥ 37፥ 49፥ 73፥ 112፥ 127፥ 128፥ 133 ናቸው። መጽሐፈ ምሳሌም እንደ እነዚህ መዝሙሮች ጥበብንና የጥበብን ሕይወት የሚያሞግስ በመሆኑ እንደ መዝሙር ልንቆጥረው እንችላለን። እነዚህ መዝሙራት ከመጽሐፈ ምሳሌ ጎን ለጎን ቢነበቡ ጠቃሚ ውጤት ይሰጣሉ (ምዕራፍ 12ን ተመልከት)።

### *የመተማመን መዝሙሮች*

እነዚህ አሥር መዝሙሮች (11፥ 16፥ 23፥ 27፥ 62፥ 63፥ 91፥ 121፥ 125፥ 131) ትኩረት ያደረጉት እግዚአብሔርን መተማመን እንደሚቻልና በመከራ ጊዜም ለሕዝቡ መልካምነቱና እንክብካቤው ሊገለጽ እንደሚገባ በሚያስረዱ አሳቦች ላይ ነው። እግዚአብሔር የሚያምኑትን ሰዎች ለሕይወታቸውና ሊሰጣቸው ለሚመርጣቸው ነገሮች በእርሱ እንደሚተማመኑ ሲያውቅ ደስ ይለዋል። በጥሩ ሁኔታ ውስጥ ብንሆንም ባንሆንም እነዚህ መዝሙሮች በእግዚአብሔር ላይ ያለንን መተማመን እንድንገልጽ ይረዱናል።

የተለያዩ የመዝሙረ ዳዊትን ምድቦች ለማጥናትና አንዱ ምድብ ከሌላው እንዴት እንደሚለይ ለማወቅ የሚፈልጉ ወገኖች «Out of the

Depths: The Psalms Speak for Us Today, 2d ed., by Bernhard Anderson (Louisville: Westminster/John Knox, 1983)» ቢያነቡ መልካም ነው። ይህ መጽሐፍ መዝሙር በጥንቷ እስራኤል እንዴት አገልግሎት ይሰጥ እንደነበረ ተጨማሪ ዝርዝሮችን ከመያዙም በላይ፥ ዛሬ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ሊያገለግል ስለሚችልባቸው መንገዶች አሳቦችን ያቀርባል።

## ሐቲታዊ ናሙና

የአንድን መዝሙር ቅርጽና መዋቅር መረዳት መልእክቱን ለመገንዘብ እንዴት እንደሚያግዝ ለማሳየት ሁለት መዝሙሮችን መርጠናል። ከእነዚህ መዝሙሮች አንደኛው የግል ሰቆቃ የተገለጸበት ሲሆን፥ ሁለተኛው የምስጋና መዝሙር ነው።

### *መዝሙር 3፡ ሰቆቃ*

ምሁራን ሁሉንም የሰቆቃ መዝሙሮች በጥንቃቄ ከመረመሩ በኋላ በሁሉም ውስጥ በጋራ ያገኙዋቸውን ስድስት ባሕርያት ለይተው ገልጸዋል። እነዚህም በተለመደው ቅደም ተከተላቸው ሲሆኑ እነዚህ ናቸው።

1. *አድራሻ፡—* መዝሙረኛው ጸሎቱን ወደ ማን እንደሚያቀርብ ይገልጻል። ይህም ለእግዚአብሔር መሆኑ ግልጽ ነው።
2. *እሮሮ፡—* መዝሙረኛው ችግሩን በመለየትና የእግዚአብሔርን እርዳታ ለምን እንደሚፈልግ በመግለጽ፥ በታማኝነትና በኃይል እሮሮውን ያሰማል።
3. *መተማመን፡—* መዝሙረኛው ወዲያው በእግዚአብሔር መተማመኑን ይገልጻል። (ቀድሞ ነገር ካልተማመንኸው ለምን ወደ እግዚአብሔር ትጮኻለህ?) የግድ አንተ በምትፈልገው መንገድ ሳይሆን፥ ተስማሚ ነው ብሎ በሚያስበው መንገድ ምላሽ እንደሚሰጥህ ልትተማመንበት ይገባል።
4. *ነፃ መውጣት(መዳን)፡—* መዝሙረኛው በእሮሮው ውስጥ ከተገለጸው ችግር እግዚአብሔር እንዲያድነው ይማጸናል።
5. *እርግጠኝነት፡—* መዝሙረኛው እግዚአብሔር እንደሚያድነው እርግጠኛ መሆኑን ይገልጻል። እርግጠኝነቱ መተማመኑን ከሚገልጽበት ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል።

6. *ምስጋና፦* መዝሙረኛው ለቀድሞው፥ ለአሁኑ እና/ወይም ለወደፊቱ በረከቶች ለእግዚአብሔር ምስጋናን፥ ውዳሴንና ክብርን ያቀርባል።

*መዝሙር 3*

እግዚአብሔር ሆይ! ጠላቶቼ ምንኛ በዙ!
ስንቱስ በእኔ ላይ ተነሣ!
ብዙዎች ነፍሴን፤ «እግዚአብሔር አይታደግሽም» አሏት።
እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን ዙሪያዬን የምትከልል ጋሻ ነህ፤
ክብሬና፤ ራሴንም ቀና ቀና የምታደርግ አንተ ነህ።
ወደ እግዚአብሔር ድምፄን ከፍ አድርጌ እጮሃለሁ፤
እርሱም ከተቀደሰ ተራራው ይመልስልኛል።
እተኛለሁ፤ አንቀላፋለሁ፤
እግዚአብሔር ደግፎ ይዞኛልና እነቃለሁ።
በየአቅጣጫው የከበበኝን፤ አእላፍ ሕዝብ አልፈራም።
እግዚአብሔር ሆይ ተነሥ!
አምላኬ ሆይ፤ ታደገኝ፤
የጠላቶቼን ሁሉ መንጋጋ ትመታለህ፤
የክፉዎችንም ጥርስ ትሰባብራለህ።
ማዳን የእግዚአብሔር ነው፤
በረከትህ በሕዝብህ ላይ ይሁን።

በዚህ መዝሙር ውስጥ ስድስቱ የሰቆቃ አላባውያን እንደሚከተለው ተለይተው ቀርበዋል።

1. *አድራሻው፦* በቁጥር 1፥ «እግዚአብሔር ሆይ» ተብሎ ተገልጾአል። አድራሻው ረዥም ወይም ባሸበረቀ ሁኔታ መቅረብ እንደማያስፈልገው አስተውል። አጫጭር ጸሎቶች እንደ ረዣዥሞቹ ሁሉ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ። እግዚአብሔርን መሸንገል የለብንም።

2. *እሮሮ፦* ይህ ከቁጥር 1 የተቀረውን ክፍልና ቁጥር 2ን ይጨምራል። ዳዊት በዚህ መዝሙር ስለ ጠላቶቹ (በእነዚህ መዝሙሮች ውስጥ የየትኛውም ችግር ተምሳሌቶች ሊሆኑ ይችላሉ) ብዛት እና ያለበትን የጨለመ ሁኔታ ይገልጻል። የትኛውም ችግር በዚህ መንገድ ሊገለጽ ይችላል።

3. *መተማመን፡-* ከቁጥር 3-6 የሚገኙት አሳቦች ሁሉ በእግዚአብሔር መተማመኑን የሚያስረዱ ናቸው። እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፥ ጸሎትን እንዴት እንደሚመልስ፥ ሁኔታቸው ተስፋ የሌለው በሚመስልበት ጊዜ ሳይቀር ሕዝቡን እንዴት እንደሚያድን ተገልጾአል። ይህ ሁሉ እግዚአብሔር ሰዎች ሊተማመኑበት የሚገባ አምላክ እንደሆነ ያሳያል።

4. *ነፃ መውጣት/መዳን፡-* ዳዊት በቁጥር 7 (እግዚአብሔር ሆይ ተነሥ! አምላኬ ሆይ ታደገኝ») የራሱን (እና የእኛን) የእርዳታ ተማጽኖ ያስተጋባል። መዝሙረኛው በእግዚአብሔር ላይ ያለውን መተማመን እስከገለጸበት ጊዜ ድረስ እንዴት የእርዳታ ጥያቄውን እንዳዘገየው ልብ በል። ይህ ቅደም ተከተል በዚህ መንገድ ካልሆነ ተብሎ የቀረበ ሳይሆን በተለምዶ የሚካሄድ ነው። በመጠየቅና በማመስገን መካከል ያለው ሚዛናዊነት የሰቆቃ መዝሙሮች መለያ የሚመስል ሲሆን፥ እኛም በራሳችን የጸሎት ሕይወት ብንጠቀምበት መልካም ነው።

5. *እርግጠኝነት፡-* ቀሪው የቁጥር 7 ክፍል /«የጠላቶቼን መንጋጋ ትሰብራለህ--- »/ እርግጠኝነትን ያመለክታል። ምናልባት «በዚህ የእግዚአብሔር የዱለኝነት ምስል ምን ዓይነት ማረጋገጫ ነው የተገለጸው?» ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። በመሠረቱ፥ ቋንቋው ግልጽ ሳይሆን ዘይቤያዊ ነው። «ጠላቶች» እና «ክፉዎች» ያን ጊዜ ዳዊት የተጋፈጣቸውንና ዛሬም እኛ የምንጋፈጣቸውን ችግሮች ስለሚያመለክቱ፥ «ቀደም ሲል እውነተኞቹን ችግሮቼን አስወግደሃል» የሚለው ትክክለኛ አገላለጽ ይሆናል። በዚህ ግልጽ ምስል፥ የሚጨቁነን ነገር እንደተሸነፈ ተገልጾአል። ነገር ግን ይህ የመዝሙር ክፍል የእግዚአብሔር ሕዝብ ከመከራ ነፃ እንደሚሆኑ ቃል እንደማይገባ አስተውል። እግዚአብሔር ለእኛ ባለው ዕቅድ መሠረት በራሱ ጊዜ ችግሮቻችንን እንደሚፈታ የሚያረጋግጥ ዋስትና ይሰጣል።

6. *ምስጋና፡-* ቁጥር 8 እግዚአብሔርን ለታማኝነቱ ያመሰግናል። እርሱ አዳኝ አምላክ የመሆኑ እውነታ የተገለጸ ሲሆን፥ ለበረከት የቀረበው ጥያቄ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚባርክ አምላክ መሆኑን ያሳያል። (ሊባርክ ከማይችል አካል በረከትን ልትጠይቅ አትችልም!)

እንደ መዝሙር 3 ካሉት የሰቆቃ መዝሙሮች ብዙ ቁም ነገሮችን መማር ይቻላል። ምናልባትም ከእነዚህ ቁም ነገሮች የሚልቀው

ሚዛናዊ ጸሎት (ልመና በምስጋና፥ እሮሮ ደግሞ በመተማመን መግለጫዎች ሚዛናዊ ሊሆን ይገባል) ሳይሆን አይቀርም። በመዝሙራት ውስጥ ግልጽነት (ዳዊት እንዴት እሮሮውንና ልመናውን በግልጽ ለማቅረብ በመንፈስ ቅዱስ እንደተነሣሣ አስተውል) መኖሩ ችግሮቻችንን ሳንሸፋፍን ለእግዚአብሔር በግልጽ እንድንናገር ያደርገናል።

ይሁንና፥ መዝሙሩ የቀረበው እንደ መሪ እንዲያገለግል እንጂ እንዲያስተምር አይደለም። ተስፋ ስንቆርጥ፥ በችግሮች ስንከበብና የሽንፈት ስሜት ሲጫነን ይህንን መዝሙር ልንጠቀም እንችላለን። ለጥንታውያን እስራኤላውያን እንዳደረገው፥ መዝሙሩ አሳባችንንና ስሜታችንን ለእግዚአብሔር እንድንገልጽና በታማኝነቱ ላይ እንድንደገፍ ያደርገናል። ምናልባትም እግዚአብሔር ይህንን መዝሙር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲገባ ያደረገው በሚያስብልን አምላካችን ላይ ጭንቀታችንን ሁሉ እየጣልን (1ኛ ጴጥ. 5፡7) ከእርሱ ጋር እንድንነጋገር ይሆናል።

አንዳንድ ጊዜ «የማኅበር ሰቆቃዎች» ተብለው የሚጠሩት የቡድን ሰቆቃዎችም እነዚህኑ ባለ ስድስት ደረጃ መስመሮች ይከተላሉ። አንድ ሰው በመዝሙር 3 በሚጠቀምበት መንገድ ቤተ ክርስቲያን ወይም ሌላ ቡድን በእነዚህ መዝሙሮች ሊጠቀም ይችላል።

*መዝሙር 138፡ የምስጋና መዝሙር*

የምስጋና መዝሙሮች የተለየ ዓላማ ስላላቸው መዋቅራቸውም ከሰቆቃ መዝሙሮች የተለየ ነው። የምስጋና መዝሙር አላባውያን የሚከተሉት ናቸው።

1. *መግቢያ፡-* እዚህ ላይ መዝሙረኛው እግዚአብሔር እንዴት እንደረዳው ጠቅለል ባለ አሳብ ይገልጻል።
2. *መከራ፡-* መዝሙረኛው እግዚአብሔር ከየትኛውም ችግር እንዳዳነው ይናገራል።
3. *ልመና፡-* መዝሙረኛው ቀደም ሲል ለእግዚአብሔር አቅርቦት የነበረውን ልመና አስታውሶ ይናገራል።
4. *ነፃ መውጣት (ደኅንነት)።* እግዚአብሔር ያሳየውን አዳኝነት ይገለጻል።
5. *ምስክርነት፡-* እግዚአብሔርን ለምሕረቱ ያመሰግነዋል።

ከዚህ አስተዋጽኦ እንደምትመለከተው፥ የምስጋና መዝሙሮች የሚያተኩሩት እግዚአብሔር ቀደም ሲል ባሳያቸው ምሕረቶች ላይ ነው። የምስጋና መዝሙር ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔርን ቀደም ሲል ላደረገው ነገር ያመሰግነዋል። የእነዚህ አምስት ነገሮች ቅደም ተከተል በምስጋና መዝሙሮች ውስጥ ሁልጊዜም በአንድ ዓይነት መልክ ላይመጣ ይችላል። በአንድ ዓይነት ቅደም ተከተል መወሰኑ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የሚጽፈውን ደራሲ የአጻጻፍ ክህሎት ሊቀንስ ይችላል።

*መዝሙር 138*

> እግዚአብሔር ሆይ፤ በፍጹም ልቤ አመሰግንሃለሁ፤
>
> በአማልክት ፊት በመዝሙር እወድስሃለሁ።
>
> ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ፣
>
> ስለ ምሕረትህና ስለ ታማኝነትህ፣
>
> ለስምህ ምስጋና አቀርባለሁ፤
>
> ስምህንና ቃልህን፣ ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አድርገሃልና።
>
> በጠራሁህ ቀን መልስ ሰጠኸኝ፤ ነፍሴን በማደፋፈርም ብርቱ አደረግኸኝ።
>
> እግዚአብሔር ሆይ፤ የአፍህን ቃል በሰሙ ጊዜ፤ የምድር ነገሥታት ሁሉ ያመስግኑህ።
>
> የእግዚአብሔር ክብር ታላቅ ነውና፣ ስለ እግዚአብሔር መንገድ ይዘምሩ።
>
> እግዚአብሔር በከፍታ ስፍራ ቢሆንም፣ ዝቅ ያለውን ይመለከተዋል፤ ትዕቢተኛውን ከሩቅ ያውቀዋል።
>
> በመከራ መካከል ብሄድም፣ አንተ ሕይወቴን ትጠብቃታለህ፤
>
> በጠላቶቼ ቁጣ ላይ እጅህን ትዘረጋለህ፤ በቀኝ እጅህም ታድነኛለህ።
>
> እግዚአብሔር በእኔ ላይ ያለውን ዓላማ ይፈጽማል፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህ ለዘላለም ነው። የእጅህንም ሥራ ቸል አትበል።

1. *መግቢያ፡–* ከቁጥር 1–2 ዳዊት እግዚአብሔር ላሳየው ፍቅርና ታማኝነት፥ ብሎም የእግዚአብሔር ታላቅነት ሊመሰገን እንደሚገባ በመግለጽ ለማመስገን መፈለጉን ያስረዳል።

2. *መከራ፡–* በቁጥር 3 ያጋጠመው ችግር ጠቅለል ባለ መልኩ ተገልጾአል። ይህ ዳዊት የእግዚአብሔርን እርዳታ የፈለገበት የትኛውም ዓይነት ችግር ሊሆን ይችላል። ይህም እግዚአብሔር

በየትኛውም በኩል የረዳው ክርስቲያን መዝሙርን እንዲጠቀም ያስችለዋል።

3. *ልመና፡–* ያቀረበውም ልመና በቁጥር 3 ተመልክቷል። ዳዊት እግዚአብሔርን የሚያመሰግነው ግልጽ አድርጎ ላልጻፈው ችግር እርዳታ በመስጠቱ ነው።

4. *መዳን፡–* ይህ ከቁጥር 6–7 በሚገባ ተገልጾአል። እግዚአብሔር ለዳዊት ልመና ትኩረት መስጠቱ፥ ከመከራ ውስጥ ሕይወቱን መታደጉ («ትጠብቃታለህ» የሚለው የአሁን ጊዜ በመሆኑ፥ ምናልባትም እግዚአብሔር ያዳነው ብዙ ጊዜ ሊሆን ይችላል) እና «ከጠላቶቹ» ማዳኑ፥ እኛም እግዚአብሔር ቀደም ሲል ላደረገልን ታማኝነት እንድናመሰግነው ያነሣሣናል።

5. *ምስክርነት፡–* ቁጥር 4–5 እና 8 ዳዊት (እና እኛም) እግዚአብሔርን የምናመሰግንበትን መሠረት ይጥላሉ። የእግዚአብሔር ክብር ታላቅ ስለሆነ የምድር ታላላቆች እንኳ ሊያመሰግኑት ይገባል (ቁ. 4–5)። የተስፋ ቃሎቹንና ፍላጎቶቹን ከመፈጸሙ ጋር በተያያዘ እግዚአብሔርን መለመንና መተማመን ይቻላል። ፍቅሩ ከቶውንም አያበቃም (ቁ.8)።

እንደ መዝሙር 138 ዓይነቱ የምስጋና መዝሙር ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ግንኙነት ታላቅን ነገር እንድንጠብቅ የሚያደፋፍር ነው። እግዚአብሔር ባለፉት ዓመታት ያሳየንን ታማኝነት ማሰላሰሉ አሳባችንና ስሜታችንን ለመቆጣጠር ምንኛ ጠቃሚ ነው!

እዚህ ከተነጋገርናቸው ይልቅ ሌሎች የመዝሙር ዓይነቶችንና ይዘቶችን ለመፈተሽ ከፈለግህ፥ ቀደም ሲል የተጠቀሰው የአንደርሰን መጽሐፍ ከፍተኛ እገዛ ያደርግልሃል። ይሁንና፥ አንድ ዓይነት ብዙ መዝሙሮችን ካነበብህ በኋላ በውስጣቸው የሚገኙትን የጋራ ባሕርያት በማውጣት ያለ ማብራሪያ መጻሕፍት እገዛም ብዙ ልትማር ትችላለህ። ዋናው ነገር መዝሙሮች በዓይነታቸው እንደሚለያዩና ዓይነቶቹን በማስተዋል መመርመሩ አስተውሎት ወደታከለበት አጠቃቀም እንደሚመራ መገንዘቡ ነው።

## ልዩ ማስታወሻ ስለ «እርግማን መዝሙሮች»

መዝሙራት በዘመናት ሁሉ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ተፈላጊዎች ሆነው ከኖሩባቸው ምክንያቶች አንዱ የቋንቋ ብቃታቸው ነው። በመዝሙራት ውስጥ ጥልቅ ሰብአዊ ስሜቶችን እናነባለን። ምንም ያህል ብታዝን መዝሙረኛው ኀዘንህን የምትገልጽባቸውን ቃላት ይሰጥሃል። ይህም ካስፈለገ እጅግ አሳፋሪ የሚመስሉ ቃላትን

የሚጨምር ነው። (ለምሳሌ፥ መዝሙር 69፡7–20፤ ወይም 88፡3–9 አንብብ።) በእነዚህ መዝሙሮች ውስጥ የሚገኘውን ከፍተኛ የግነት ቋንቋ ቸል ማለቱ አስቸጋሪ ነው።

ኃዘንና ደስታ ኃጢአት አይደሉም። ነገር ግን እንደ መራርነት፥ ቁጣና ጥላቻ የመሳሰሉት ስሜቶች አንድን ሰው ወደ ኃጢአት ተግባራት ሊመሩ ይችላሉ። እነዚህም ሌሎችን የመጉዳት ፍላጎት ወይም ሙከራ የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። ቁጣን በቃላት መግለጹ የጭካኔ ተግባራት ከመፈጸም የተሻለ ነው። አንዳንድ መዝሙሮች በእነዚህና በሌሎችም ተጨማሪ መንገዶች ይረዱናል። ቁጣችንን በቃልም ሆነ በአካላዊ ሁኔታ ወደ ማንም ሰው እንዳናነጣጥርና ወደ እግዚአብሔር በቃላት እንድናስተጋባ ይመሩናል። ቁጣን ለእግዚአብሔር የሚገልጹ መዝሙሮች የእርግማን መዝሙሮች ይባላሉ።

አንዳንድ ጊዜ ለሌሎች ሰዎች አሉታዊ አሳቦች አይኖሩንም ማለት ውሸት ነው። በሌሎች ሰዎች ላይ ኃጢአትም ሆኑ ኃጢአት ያልሆኑ አሉታዊ አሳቦች ይኖሩናል። እግዚአብሔር በርግማን መዝሙሮች አማካኝነት እንድንቆጣና ኃጢአትን እንዳናደርግ ይጋብዘናል (መዝ. 4፡4)። «ተቆጡ፤ ነገር ግን ኀጢአት አትሥሩ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፤ ለዲያብሎስም ስፍራ አትስጡት» (ኤፌ. 4፡25–26) የሚለውን የአዲስ ኪዳን ትምህርት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል። ይህንንም የምናደርገው ክፉት ለፈጸሙብን ክፉት ከመመለስ ይልቅ ቁጣችንን በቀጥታ ለእግዚአብሔር በመግለጽ ነው። የእርግማን መዝሙሮች ከሌሎች የመዝሙር ዓይነቶች የምናውቃቸውን ግልጽ፥ ዓላማ ያላቸው ግነቶችን በመጠቀም ቁጣችንን ተቆጣጥረን ለእግዚአብሔር እንድንገልጽ ይረዱናል።

ብዙውን ጊዜ የእርግማን መዝሙሮች የሚገኙት በሰቆቃ መዝሙሮች ውስጥ ነው። ከላይ በዝርዝር በተመለከትነው መዝሙር 3 ውስጥ በቁጥር 7 እንደ አብዛኞቹ ሌሎች ክፍሎች አጠር ያለ የእርግማን አሳብ የሚገኝ ሲሆን፥ ይህም አጭርነት እጅግ አስቀያሚ እንዳይሆን ያደርገዋል። አንዳንድ የእርግማን መዝሙሮች ግን ረዣዥምና ከረር ያሉ ናቸው። (በመዝሙር 12፥ 35፥ 58፥ 59፥ 69፥ 70፥ 83፥ 109፥ 137፥ 140 ውስጥ ያሉትን የእርግማን ክፍሎች አንብብ።) ለምሳሌ ያህል፥ መዝሙር 137፡7–9 ተመልከት።

እግዚአብሔር ሆይ፤ ኢየሩሳሌም በወደቀችበት ቀን፤

ኤዶማውያን እንዴት እንደ ዛቱ አስብ፤

ደግሞም፤ «አፍርሷት፤ ፈጽማችሁ አፈራርሷት» አሉ።

አንቺ አጥፊ የሆንሽ የባቢሎን ልጅ ሆይ፤

በእኛ ላይ ስለፈጸምሽው ድርጊት፤

የእጅሽን የሚሰጥሽ የተመሰገነ ነው፤

ሕፃናትሽንም ይዞ የሚፈጠፍጥ የተመሰገነ ነው።

መዝሙር 137 እስራኤላውያን በምርኮ መሠቃየታቸውን የሚገልጽ የሰቆቃ መዝሙር ነው። መዲናቸው ኢየሩሳሌም የወደመች ስትሆን፥ ባቢሎናውያን በኤዶማውያን እገዛ አገራቸውን ወስደውባቸው ነበር። (የአብድዩን መጽሐፍ አንብብ።) «በቀል የእኔ ነው፤ እኔ እከፍላለሁ» የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል በማሰብ (ዘዳግ. 32፡35ን ከሮሜ 12፡19 ጋር አነጻጽር)፥ የዚህ ሰቆቃ አዘጋጅ *በቃል ኪዳኑ እርግማን መሠረት* (ምዕ. 10ን አንብብ) ፍርድ እንዲመጣ ይጣራል። በእነዚህ እርግማኖች ውስጥ ጠቅላላው ክፉ ማኅበረሰብ ከቤተሰቡ አባላት ጋር እንዲጠፉ የሚጠይቅ አሳብ ቀርቧል። (ዘዳግ. 32፡25ን ከ28፡53–57 ጋር አነጻጽር።) ይሁንና፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ጊዜያዊ ፍርድ ለእነዚህ የቤተሰብ አባላት የዘላለማዊ ፍርድን ውሳኔ እንደሚያመለክት የሚገልጽ አሳብ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ አይገኝም።

በመዝሙር 137 መዝሙረኛው ያደረገው ነገር ቢኖር፥ በቃል ኪዳን እርግማኖች ውስጥ የሚገኙትን የግነት ቋንቋዎች በመጠቀም በመከራ ውስጥ ያሉትን እስራኤላውያን ስሜት ለእግዚአብሔር መናገር ነበር። መዝሙረኛው በቀጥታ ለባቢሎናውያን የሚናገር የሚመስለው ከመዝሙሩ የአቀራረብ ስልት አንጻር ነው። በቁጥር 5 ደግሞ ለኢየሩሳሌምም በቀጥታ ይናገራል። የእነዚህ የቁጣ ቃላት ሰሚ እግዚአብሔር ብቻ ነው (ቁ. 7)። የእኛንም የቁጣ ቃላት ሊሰማ የሚገባው አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እንደ ሰቆቃ መዝሙር አካላት በዓውዳቸው ውስጥ እውቅና ካገኙና የኃጢአት እርሾ–አዘል ሊሆን የሚችል ቁጣችንን ለመቆጣጠር በአግባቡ ካገለገሉ፥ የእርግማን መዝሙሮች ከኃጢአት ሊጠብቁን ይችላሉ። በሌሎች ላይ መቆጣት ሁላችንም ልናስወግደው የሚገባን ነገር ነው (ማቴ. 5፡22)።

የእርግማን መዝሙሮች እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ክርስቶስ የሰጠንን ትምህርት አይቃረኑም። ብዙውን ጊዜ ፍቅርን ለሌሎች ሰዎች የተሟሟቀ ስሜት ከማሳየት ጋር እኩል በማድረግ እንሳሳታለን። ነገር ግን በክርስቶስ ትምህርት የፍቅር ፍች ተግባራዊነትን ያመላክተ ነው። ፍቅርን የሚያሳየው ለአንድ ሰው የምታሳየው ስሜት ሳይሆን፥ የምታከናውንለት ተግባር ነው (ሉቃስ 10፡25–37)። መጽሐፍ ቅዱስ

አዛኝ የሆነ የፍቅር ስሜት እንዲኖረን ሳይሆን፥ ፍቅርን ተግባራዊ እንድናደርግ ያዘናል። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ የእርግማን መዝሙሮች የቁጣ ስሜት በሚሰማን ጊዜ፥ ቁጣችንን ተግባራዊ እንዳናደርግ ይረዱናል። ምንም ያህል የምሬትና የጥላቻ ስሜት ቢሰማንም ቁጣችንን ለእግዚአብሔር በመግለጽ፥ እግዚአብሔር በበደሉን ሰዎች ላይ የፍትሕ እርምጃ እንዲወስድ ለእርሱ አሳልፈን እንሰጣለን። ትዕግሥታችንን ንቆ በክፋቱ የሚገፋ ጠላት ራሱን አጣብቂኝ ውስጥ እንደሚከት መገንዘብ ይኖበታል (ሮሜ 12፡21)።

የመጨረሻ ቃል፦ በመዝሙራት ውስጥ «ጥላቻ» የሚለው ቃል የተሳሳተ ፍች ሲሰጠው ኖሯል። መዝሙረኛው «በፍጹም ጥላቻ ጠልቻቸዋለሁ» [መዝ. (139)፡22] ሲል፥ ኃጢአትን መግለጹ አልነበረም። እንደዚያ ከሆነማ እግዚአብሔር፥ «ዔሳውን ጠላሁ» (ሚልክ. 1፡2ን ከሮሜ 9፡13 ጋር አነጻጽር) ሲል ኃጢአት ሠርቷል ልንል ነው ማለት ነው። «ጥላቻ» ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል በአንዳንድ ዓውዶች ውስጥ «ንቀት» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። እንዲሁም ደግሞ «ለመታገሥ አለመቻል ወይም አለመፍቀድ» ወይም «መተው፣ ማግለል» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። እነዚህ ሁለቱም የዕብራይስጥ መዝገበ ቃላት የሚያስቀምጧቸው መደበኛ አተረጓጎሞች ናቸው። ከዚህ አንጻር፥ የእርግማን መዝሙራት ቋንቋዎች ማቴዎስ 5፡22ን ጨምሮ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ይጣረሳሉ ማለት አይቻልም።

## ለሥነ አፈታታዊ ምልከታዎች አንዳንድ የማጠቃለያ አሳቦች

ለብዙ ትውልዶች ያህል ክርስቲያኖች በችግር፥ ግራ በመጋባት ወይም በደስታ ጊዜ በደመነፍስ ፊታቸውን ወደ መዝሙር ዳዊት ሲመልሱ ስለሆኑ፥ ለዚህ መጽሐፍ አሁንዚያዊ መርሆዎችን ለመስጠት አንደፍርም። ለዚህም ምክንያቱ ምናልባት የአንባብያኑን ፍላጎት እንዳናደበዝዝ ነው። ይህም ሆኖ መዝሙረ ዳዊትን ለማንበብ፥ ለመዘመር ወይም ለመጸለይ የበለጠ እገዛ ያደርጋሉ ያልናቸውን አሳቦች ቀጥለን እናቀርባለን።

በመጀመሪያ፥ ክርስቲያናዊ «ደመ ነፍስ» (የጋራ ግንዛቤ) ይህንን ምዕራፍ ለከፈትንበት ጥያቄ (እነዚህ ለእግዚአብሔር የተነገሩት ቃላት ለእኛ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚያገለግሉት እንዴት ነው?) መሠረታዊ ምላሽ እንደሚሰጥ መገንዘብ አለብን። የጥያቄው ምላሽ ለእስራኤላውያን ያገለገሉባቸውን መንገዶች የሚዳስስ ነው። ይኸውም ቀደም ሲል ሌሎች እንዲናገሩ በእስትንፋሱ ባነሣሣቸው ቃላት

አማካኝነት ለእግዚአብሔር የመናገር ዕድል የሚሰጡን መሆናቸው ነው።

## *የመዝሙራት ሦስት ዐበይት ጥቅሞች*

በጥንቷ እስራኤልና በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ከታየው የመዝሙራት አገልግሎት በመነሣት ዛሬ ክርስቲያኖች ሊጠቀሙ የሚችሉባቸውን ሦስት ጠቃሚ መንገዶች ልንመለከት እንችላለን። በመጀመሪያ ደረጃ፥ መዝሙራት *የአምልኮ መመሪያዎች* መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል። ይህን ስንል እግዚአብሔርን ለማመስገን፥ ለመለመን፥ ወይም በረከቶቹን ለማስታወስ የሚፈልግ አምላኪ አሳቦቹንና ስሜቶቹን ለመግለጽ መዝሙራትን እንደ መደበኛ መንገዶች ሊጠቀምባቸው ይችላል ማለታችን ነው። መዝሙራት ለንግግር የተዘጋጁ ቃላት በጥንቃቄ የቀረቡበት ሥነ ጽሑፋዊ ስልት ነው። አንድን መዝሙር ለጌታ ለመግለጽ የምንፈልገውን አሳብ የሚነካ ሆኖ ሲገኝ፥ በዚያ መዝሙር ረዳትነት አሳባችንን በጥሩ ሁኔታ ልንገልጽ እንችላለን። ራሳችን ትክክለኞቹን ቃላት ለማግኘት ስለምንቸገር፥ ችግሮቻችንን በአግባቡ ለመግለጽ ይረዳናል።

ሁለተኛ፥ መዝሙራት ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት *በታማኝነት እንደምንዛመድ* ያሳዩናል። ምንም እንኳ በዚህ ነጥብ ላይ ብዙ ዶክትሪናዊ ትምህርት ባይሰጡም፥ እውነተኛውን ትምህርት በምሳሌ ያስተምሩናል። ከመዝሙራት ውስጥ ደስታን፥ ቅያሜን፥ ቁጣን ወይም ሌሎች ስሜቶችን እንዴት በግልጽ ማሳየት እንደሚቻል እንማራለን።

ሦስተኛ፥ መዝሙራት እግዚአብሔር ስላደረገልን ነገር *የማሰብንና የማሰላሰልን* አስፈላጊነት ያስተምሩናል። መዝሙራት ለጸሎት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለማሰብና ከሌሎች አማኞች ጋር ማሰላሰል የታከለበትን ኅብረት እንድናመቻች ይጋብዙናል። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ደግሞ በሕይወታችን ውስጥ የንጽሕናንና የቸርነትን ሕይወት ይቀርፃሉ። መዝሙራት ከሌሎች የሥነ ጽሑፍ ቅርጾች ይልቅ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ወደምናደርግበት ስፍራ ከፍ በማድረግ፥ የመንግሥቱን ትላቅነትና ለዘላለም ከእርሱ ጋር መኖር እንደሚመስል እንድናስብ ይረዱናል። ሕይወት ልንታገሠው የማንችል ጨለማ በሚሆንባቸው ጊዜያት ሳይቀር እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው። ከስሜቶቻችን ባሻገር ልንተማመንበት እንደምንችል ስለምናውቅ፥ የጌታን ማዳን ከጥልቁ ሆነን እንጠባበቃለን [መዝ. (130)፡1]። ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር መጮኽ በታማኝነቱ ላይ መፍረድ ሳይሆን፥ ታማኝነቱን ማጽናት ነው።

## *ማስጠንቀቂያ*

ይህንን ምዕራፍ የምናጠቃልለው ከአንድ ጠቃሚ ማስጠንቀቂያ ጋር ይሆናል። ይኸውም *መዝሙራት ለመልካም ሕይወት ዋስትና እንደማይሰጡ ነው።* በአንዳንድ መዝሙሮች ላይ እግዚአብሔር የአማኞችን ሕይወት ደስተኛና ከመከራ የጠራ ለማድረግ ቃል መግባቱን መጥቀሱ፥ የመዝሙራትን ቋንቋ አለመረዳትና ከሚገባው በላይ አሳቡን በቀጥታ መውሰድ ይሆናል። በመዝሙራት ውስጥ በታላላቅ ቃላት የእግዚአብሔርን በረከት የገለጸው ዳዊት 1ኛና ሁለተኛ ሳሙኤል እንደገለጹት፥ ኀዘንና ችግር ያልተለየው ሕይወት ለመኖር ተገዶአል። ይሁንና፥ በሰቆቃው ጊዜም እንኳ ቢሆን ሁልጊዜም እግዚአብሔርን በጋለ መንፈስ ሲያመሰግን እንመለከታለን። ይህም ጳውሎስ በመከራም ጊዜ እግዚአብሔርን እንድናመሰግን ከመከረን አሳብ ጋር ተመሳሳይ ነው (ኤፌ. 1፡16፤ 5፡20)። ከመከራችን ባሻገር፥ በመከራችን ውስጥ ሆነን እግዚአብሔርን ለታላቅነቱና ለመልካምነቱ ልናመሰግነው ይገባል። ምክንያቱም ይህ ሕይወት ከመከራ ነፃ የመሆን ዋስትና የለውምና።